# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

# በእንስሳትና አሳ ሀብት ልማት ሚኒስቴር የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ መቆጣጠሪያና ማጥፊያ ኢኒስቲትዩት



# የደቡብ ኢትዮጵያ ስምጥ ሸለቆ የቆላ ዝንብ ማጥፊያ አፈፃፀምን በተመለከተ የተከናወነ የክትትል ኦዲት /FOLLOW UP AUDIT/ ሪፖርት

ሰኔ 2008 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# ማ ው ጫ

ክፍልአንድ ........ 1
መግቢያ ........ 1
የኢኒስቲትዩቱራዕይናተልዕኮ ........ 4
ራዕይ ........ 4
ተልዕኮ ........ 4
የኢኒስቲትዩቱስልጣንናተግባር ........ 4
የኢኒስቲትዩቱአደረጃጀት ........ 6
የክትትልኦዲቱዓላማ ........ 6
የክትትልኦዲቱወሰንእናዘዴ ........ 7
የክትትልኦዲቱመመዘኛመስፈርቶች (Standards of follow up Audit) ........ 7
ክፍልሁለት ........ 8
በክትትልኦዲትወቅትየተገኙየኦዲትግኝቶች ........ 8
በኢኒስቲትዩቱበየዓመቱየሚዘጋጁእቅድናየእቅድአፈፃፀምንበተመለከተ፡- ........ 12
ኢኒስቲትዩቱየተያዘለትበጀትአጠቃቀምእናለኢኒስቲትዩቱየሚያስፈልጉመሳሪያዎችናመድኃኒቶችግዢንበተመለከተ፡- ........ 15
በኢኒስቲትዩቱየንብረትአያያዝ፣አወጋገድእናተገዝተውያለአገልግሎትየተቀመጡንብረቶችንበተመለከተ፡- ........ 20
በመስክስራላይየሚሳተፉማህበረሰቦችንመምረጫመስፈርትንበተመለከተእናበኢኒስቲትዩቱለሚረቡዝንቦችምሆነለመስክአገልግሎትየሚውሉመሳሪያዎችስለመሟላታቸው፡- ........ 31
ለቆላዝንበእርባታየተሰሩክፍሎችን /ሞጁልስ/ እናበቆላዝንብአካባቢየሚኖረውማህበረሰብናአከባቢስላገኘውጥቅምናጉዳትጥናትመደረጉንበተመለከተ፡- ........ 35
በእንስሳትጀርባላይየሚቀባኬሚካልመጠንአጠቃቀምስርዓትስለመዘርጋቱ፡- ........ 38
በቆላዝንብንለማጥፋትለሚሳተፉየማህበረሰብአካላትየሚሰጥስልጠናንእናለእንስሳትመቀቢያየሚያገለግሉበአካባቢውከሚገኙቁሳቁሶችየተሰሩበረቶችንበተመለከተ፡- ........ 43
በኢኒስቲትዩቱየተጠናከረየመረጃአያያዝስለመኖሩእናበቆላዝንቦችእርባታወቅትለሚከሰቱየሞትአደጋዎችመንስኤእናየመፍትሄሃሳቦችበመረጃስለመያዙ፡- ........ 47
ከባለድርሻአካላትጋርስለሚደረግየመረጃልውውጥ፡- ........ 50
ክፍልሦስት ........ 54
መደምደሚያ ........ 54
ክፍልአራት ........ 57
የማሻሻያሃሳቦች ........ 57

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

1.የኢትጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ መንግስት የሀገራችንን የድህነት ገፅታ ለመለወጥና መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገሮች ተርታ እንድትሰለፍ ለማድረግ የግብርናና ገጠር ልማትን ጨምሮ የተለያዩ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎችን ቀርፆ ለተግባራዊነታቸው ከፍተኛ ርብርብ እያደረገ ይገኛል፡፡የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ መሰረቱ ግብርና እንደመሆኑ መጠን ከአገሪቱ አጠቃላይ ምርት ከፍተኛ ድርሻ የሚይዘው የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚው ነው፡ ፡ ግብርናው ዋና መሰረቶችም የሰብል ምርትና የእንስሳት ሀብታችን ናቸው፡፡ሀገራችን የበርካታ እንስሳት ሀብት ባለቤት ስትሆን እንስሳቱ ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ ሀብት የሚያበረክቱት ድርሻ ከፍተኛ ነው፡፡በመሆኑም የእንስሳት ሀብታችን የህብረተሰቡ የኑሮ መሰረትና የሀገሪቱ ኢኮኖሚ የማዕዘን ድንጋይ ናቸው፡፡ ሆኖም ግን የእንስሳት ሀብታችን ለሀገሪቱ አጠቃላይ የግብርና ምርት ብሎም የሀገሪቱ ኢኮኖሚ እድገት የጎላ አስተዋፅኦ የሚያበረክት ቢሆንም በተጨባጭ እያስገኘ ያለው ጠቀሜታ ሀገሪቱ ካላት የእንስሳት ሀብት አንፃር ዝቅተኛ ነው፡፡ ለዚህም በርካታ መንስኤዎችን መጥቀስ የሚቻል ሲሆን ከእንስሳት ጤና ጋር በተያያዘ ያለው ችግር ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛል፡፡በአገራችን የእንስሳት ሀብትና ኢኮኖሚ ላይ ከፍተኛ ጉዳት በማስከተል ከሚታወቁ ዋና ዋና በሽታዎች መካከልም የገንዲ በሽታ አንዱ ነው፡፡

2.የቆላ ዝንብ ከሰሃራ በታች ባሉ 37 የአፍሪካ ሀገሮች ተሰራጭቶ የሚገኝ ሲሆን 23 ያህል ዝርያዎች ተለይተው የታወቁ መሆኑ ተገልጿል፡፡እነዚህ የቆላ ዝንብ ዝርያዎች በሰው ላይ በአፍሪካ የእንቅልፍ በሽታ /sleeping sickness/ እንዲሁምበእንስሳት ላይ ገንዲ /naganeng/ የተባሉትን በሽታዎች በማስተላለፍ ከፍተኛ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖ በማድረስ ላይ መሆናቸው ተገልጿል፡፡

3. በኢትዮጵያም የቆላ ዝንብ ባለበት አካባቢ ሰፍረው የሚኖሩ ህዝቦችም በዚሁ በቆላ ዝንብ በሚተላለፈው የገንዲ በሽታ ምክንያት የቀንድ ከብቶቻቸውና ሌሎች የቤት እንስሳቶቻቸው ምርታማ ሊሆኑ ባለመቻላቸው ያላቸው የእንስሳት ሀብት ሊኖራቸው ከሚችለው ጋር ሲነፃፀር አነስተኛ ከመሆኑም በላይ ከእንስሳት ሀብት የሚያገኙት

ውጤትም እንደዚሁ ከሚጠበቀው በታች መሆኑ በጥናት ሰነዶች ተመልክቷል፡፡ በተጨማሪም የቀንድ ከብቶችን በመጠቀም በአካባቢው የእርሻ ልማት ለማካሄድ የሚደረገውን ጥረት በሽታውን የሚያስተላልፈው የቆላ ዝንብ መኖሩ የእርሻ ከብቶች ለገንዲ በሽታ መጋለጥ ከፍተኛተፅዕኖ አድርሶበታል፡፡

4. የገንዲ በሽታን ለመቆጣጠር በአገራችን የተለያየ ጥረት ሲደረግ የቆየ ቢሆንም፤ጥረቶቹ በአብዛኛው ያተኮሩት ለበሽታው መፈወሻ የሚሆን መድሀኒት በመጠቀም ነበር፡፡በዚህም ምክንያት መድሀኒቶቹ ለረዥም ጊዜ በጥቅም ላይ በመዋላቸውና አልፎ አልፎ በአግባቡብ ጥቅም ላይ ባለመዋላቸው በአንዳንድ አካባቢዎች በሽታው መድሀኒቶቹን የመላመድና የመቋቋም ሁኔታ በማሳየት ላይ ይገኛሉ፡፡

5 በመሆኑም በሽታውን በመድሀኒት ከመቆጣጠር በተጨማሪ የበሽታው አስተላላፊ የሆነውን የቆላ ዝንብ ለመቆጣጠር የሚያስችል ዘዴ ተግባራዊ ተደርጐ ቆይቷል፡፡ ይህም ዘዴ በአመዛኙ የዝንቧን ብዛት በፀረ ዝንብ ኬሚካል የመቀነስ አካሄድ ሲሆን፤ በተወሰኑ ቦታዎች ደግሞ የዝንብ ወጥመድ (Trap) በመጠቀም ጭምር ሲከናወን ቆይቷል፡፡ ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው እስካሁን ለረዥም ጊዜያት የተሰሩት ስራዎች በበሽታውም ሆነ በሽታውን በምታስተላልፈው ዝንብ ላይ የተወሰዱት እርምጃዎች በቁጥጥር ላይ እንጂ በማጥፋት ላይ ያላተኮሩ እንደነበሩ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ከተገኙ ሰነዶች እና መግለጫዎች ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

6. ከዚህም በመነሳት የገንዲን በሽታና አስተላላፊ የሆነውን የቆላ ዝንብ ለማስወገድ የሚያስችል ነፍሳትን የማምከን ቴክኖሎጂ በተለያዩ የሰሜንና መካከለኛው አሜሪካ፣ በእስያ እንዲሁም በሰሜንና ምስራቅ አፍሪካ የፍራፍሬ ተባይና የእንስሳት በሽታ አስተላላፊ የሆኑ ዝንቦችን ለማጥፋት በሚደረግ ጥረት ላይ ተግባራዊ ሁነው ውጤታማነቱ ተረጋግጧል፡፡

7. በመሆኑም ይህን አዲስ ቴክኖሎጂ ስራ ላይ ለማዋልና በሀገራችንም የቆላ ዝንብን ለማጥፋት በሚያስችል ነፍሳትን የማምከን ቴክኖሎጂ (The Sterile Insect Technique) አጠቃቀም አቅም በብሔራዊ ደረጃ ለመገንባትና በደቡብ ኢትዮጵያ ስምጥ ሸለቆ ውስጥ 25,000 ካሬ ኪሎ ሜትር ስፋት ያለው ቦታ ከገንዲ በሽታ እና ቆላ ዝንብ ነፃ ለማድረግ የደቡብ ኢትዮጵያ ስምጥ ሸለቆ የቆላ ዝንብ ማጥፊያ ፕሮጀክት በ1990 ዓ.ም

በኢትዮጵያ መንግስትና በአለም አቀፍ አቶሚክ ኢነርጂ ኤጀንሲ መካከል በተደረገ የጋራ ስምምነት ተቋቁሞ የቆላ ዝንብን ከ1990 ዓ.ም ጀምሮ ባሉት 10 ዓመታት ድረስ ለማጥፋት ፕሮጀክት ተቀርጾ ትግበራ ላይ የሚገኝ ነው፡፡

8. ፕሮጀክቱም ለአገራችን በአይነቱ የመጀመሪያ የሆነውን የነፍሳት ማምከን ቴክኖሎጂን ሥራ ላይ በማዋል በአጠቃላይ በአገሪቱ የቆላ ዝንብ ከሚገኝበት 240,000 ካሬ.ኪ.ሜ ውስጥ በደቡብ ኢትዮጵያ ስምጥ ሸለቆ የሚገኘውን 25,000 ካሬ.ኪ.ሜ ስፋት ላይ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ማፅዳት፣ እንዲሁም 60,000 ካሬ.ኪ.ሜ በሚሆን ተጨማሪ አከባቢ የቁጥጥሩን ስራ በመጀመር ችግሩን ከ 90-95% መቀነስ እና የቆላ ዝንብ ቅነሳ ከተካሄደባቸው አከባቢዎች በ 1000 ካሬ.ኪ.ሜ የመከኑ ወንድ የቆላ ዝንቦችን በመልቀቅ በቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ የተጠቁ አከባቢዎች ለእንስሳት እርባታና እርሻ ልማት ምቹ እንዲሆኑ ለማድረግ ነው፡፡

9. መንግስት ብሔራዊ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ መቆጣጠሪያና ማጥፊያ ኢኒስቲትዩትን በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 304/2006 የካቲት 20/2006 ዓ/ም በወጣው 20ኛው ዓመት የኢፌዲሪ ነጋሪት ጋዜጣ ቁጥር 26 መሰረት በማቋቋም ችግሩ ባለባቸው አምስት ብሄራዊ ክልሎች ተግባራዊ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ ኢኒስቲትዩቱ በ 2008 በጀት ዓመት በስሩ የሚገኙ ማዕከላት ማለትም ቃሊቲ የቆላ ዝንብ ማራቢያና ማምከኛ ማዕከል፣ አርባምንጭ የቆላ ዝንብ ገንዲ በሽታ መቆጣጠሪያና ማጥፊያ ማዕከል እና በደሌ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ መቆጣጠሪያና ማጥፊያ ማዕከል ሠራተኞችን በአዲስ መልክ አደራጅቶ እንቅስቃሴ ላይ ይገኛል፡፡

## የኢኒስቲትዩቱ ራዕይና ተልዕኮ

### ራዕይ

9. የገንዲ በሽታን በመቆጣጠርና በማጥፋት የእንስሳትና የሰብል ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ አርሶ አደሩና አርብቶ አደሩን ተጠቃሚ በማድረግ እድገቷን ያስቀጠለች ኢትዮጵያን ማየት፤

### ተልዕኮ

10. የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን በማቀናጀትና ህብረተሰቡን በስፋት በማሳተፍ በቆላ ዝንብና በገንዲ በሽታ የተጠቁ አከባቢዎችን ከችግሩ ነፃ በማድረግ ለእንስሳት እርባታና ለግብርና ልማት ምቹ ሁኔታ መፍጠር የሚሉ ናቸው፡፡

## የኢኒስቲትዩቱ ስልጣንና ተግባር

11. የኢኒስቲትዩቱ ስልጣንና ተግባራት ፡-

- በቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቁጥጥርና ማጥፋት ሥራ የሚያስፈልጉ ቴክኖሎጂዎችን ይለያል፣ ይገመግማል፣ ይመዝናል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፣ ችግር ፈቺ ጥናትና ምርምሮችን ያካሂዳል፣
- ከቆላ ዝንብና ከገንዲ  በሽታ ቁጥጥርና ማጥፋት ጋር በተያያዘ መመሪያዎችን ያወጣል፣
- በቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ የተጠቁ አካባቢዎችን በመለየት ለስራ በሚያመች መልኩ ያደራጃል፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበርም ይሠራል፣
- በቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቁጥጥርና ማጥፋት ስራ ያልሆኑት ማዕከል በመሆን የአገር ውስጥና ዓለም አቀፍ ስልጠናዎችና የአቅም ማጎልበቻ መርሃ ግብሮችን ያዘጋጃል፣
- ለቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቁጥጥር የሚያስፈልጉ ኬሚሎች፣ የላብራቶሪ ዕቃዎች፣ የመስክ መገልገያዎች፣ ቋሚ ዕቃዎችና አላቂ ዕቃዎች ስፔስፊኬሽን ያዘጋጃል፣

- የአገልግሎት አሰጣጡን ለማቀላጠፍና ለማስፋፋት የሚረዱ ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል፣
- በዘርፉ የተሻለ ልምድና ተሞክሮ ካላቸዉ የአገር ውስጥና ዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር ጠንካራ ግንኙነት በመፍጠር አቅሙን ይገነባል፣
- አሠራሩን ለማቀላጠፍና ለማጠናከር በቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ዘርፍ የተደረጉ አዳዲስ ሳይንሳዊ ግኝቶችን ከአገሪቱ ተጨባጭ ሀኔታ ጋር በማገናዘብና በማጣጣም ጥቅም ላይ ያውላል፣
- የቆላ ዝንብ፣ የገንዲ በሽታ፣ የሶሾ-ኢኮኖሚና አካባቢያዊ ሁኔታ መረጃ ይሰበስባል፣ መረጃውን መሠረት በማድረግ:-

  ሀ/ የቁጥጥር ዘዴዎችና ስልቶችን ይለያል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፣ ውጤቱን ይገመግማል፣

  ለ/ በዘርፉ የመረጃ ማዕከል ሆኖ ያገለግላል፣ የወቅታዊ መረጃዎች ተደራሽነትን ያረጋግጣል፣

  ሐ/እንደአስፈላጊነቱ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታመረጃዎችን ለባለሙያዎች፣ ለተመራማሪዎች፣ ለባለድርሻ አካላትና ለሌሎች ተጠቃሚዎች ያሰራጫል፣

- ለእርባታና ለምርምር የሚሆኑ ዝንቦችና ሌሎች ባዮሎጂካል ውጤቶች የአገሪቱ ሕግ በሚፈቅደው መሠረት ወደ አገር ውስጥ ያስገባል፣ ይጠቀማል፣ ወደ ውጭ አገርም ይልካል፣
- ከቆላ ዝንብ ዕርባታ፣ የጥራት ቁጥጥርና ምርምር በማካሄድ ብቁና ተወዳዳሪ የሆኑ ወንድ የቆላ ዝንቦችን ያመርታል፣ አምክኖ መስክ ላይ ይለቃል፣ ይከታተላል፣
- ከቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቁጥጥር ጋር በተያየዘ መሥራት የሚፈልጉ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ሊሳተፊ የሚችሉበት መስፈርት ያዘጋጃል፣ በመስፈርቱ መሰረት እንዲሰተፊ ይፈቅዳል፣ ክትትልና ግምገማ ያደርጋል፣ ከመስፈርቱ ውጭ የሚሰሩትን ያግዳል፣

- ለቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቁጥጥር ወይም ለላብራቶሪ አገልግሎት የሚውሉ ኬሚካሎችና መድሃኒቶች የአገልግሎት ጊዜያቸው ከማብቃቱ በፊት ሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ የአገልግሎት ጊዜያቸው ያለፈባቸውን ኬሚካሎችና መድሃኒቶች ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን እንዲወገዱ የደርጋል፣
- የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በራሱ ስም ይከሳል፣ ይከሰሳል፣
- ዓላማውን ለማስፈፀም የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## የኢኒስቲትዩቱ አደረጃጀት

12. ኢኒስቲትዩቱ በአንድ ዋና ዳይሬክተር የሚመራ ሲሆን፣በስሩ የቃሊቲ የቆላ ዝንብ ማራቢያና ማምከኛ ማዕከል፣ የአርባምንጭ የቆላ ዝንብ ገንዲ በሽታ መቆጣጠሪያናማጥፊያ ማዕከል እና የበደሌ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ መቆጣጠሪያና ማጥፊያ ማዕከል ሲኖሩት በአርባምንጭ የቆላ ዝንብ ገንዲ በሽታ መቆጣጠሪያና ማጥፊያ ማዕከልስር ደግሞ የዲላ ጣቢያ፣ የወላይታ ሶዶ ጣቢያ እና የአርባምንጭ ጣቢያ ያሉትና ተጠሪነቱም ለእንስሳት እና ዓሣ ሀብት ልማት ሚኒስቴር ሲሆን፣ በሶስት ዋና የስራ ሂደቶች (የቆላ ዝንቦች ለማጥፋት የሚያስችል የአቅም ግንባታ፣ የመስክ ኦፕሬሽን እና የተቀናጀ ቴክኖሎጂን በመጠቀም የቆላ ዝንብን የማጥፋት ዋና የስራ ሂደቶች) እና በስድስት ደጋፊ የስራ ሂደቶች (የሰው ሀብት ስራ አመራር፣ የፋይናንስ፣ አቅርቦትና ንብረት አስተዳደር፣ የፕላንና ፕሮግራም፣ የውስጥ ኦዲት እና ህዝብ ግንኙነት ደጋፊ የስራ ሂደቶች) የተደራጀ ነው፡፡

## የክትትል ኦዲቱ ዓላማ

13. የክትትል ኦዲቱ ዓላማ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በ 2003/2004 ዓ.ም የቆላ ዝንብና የገንዲ በሽታ መቆጣጠሪያና ማጥፊያ ኢኒስቲትዩት ላይየደቡብ ኢትዮጵያ ስምጥ ሸለቆ የቆላ ዝንብ ማጥፊያ ፕሮጀክት አፈፃፀምን በተመለከተ ባካሄደው የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት መሰረት በተገኙ ግኝቶች ላይ የተሰጡት የማሻሻያ ሀሳቦች፣ እንዲሁም የተሰጡትን ማሻሻያ ሀሳቦች ተግባራዊ በማድረግ የክዋኔ ኦዲቱ ያመጣውን ውጤትና ያስገኘውን ጥቅም መገምገም እንዲሁም እስካሁን ያልተቀረፉ ችግሮች ካሉ ምክንያቱን በማየትና በማጣራት ችግሮች እንዲቀረፉ የማሻሻያ ሃሳብ መስጠት ነው፡፡

## የክትትል ኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ

14. የክትትል ኦዲቱ የሸፈነው ከ2005-2008 ዓ.ም ያሉትን የሶስት በጀት ዓመታት እና የ2008 ዓ.ምየግማሽ ዓመት የሥራ ክንውኖችን እንቅስቃሴ መሰረት ባደረገ በቆላ ዝንብና የገንዲ በሽታ መቆጣጠሪያና ማጥፊያ ኢኒስቲቲዩት የደቡብ ኢትዮጵያ ስምጥ ሸለቆ የቆላ ዝንብ ማጥፊያ ፕሮጀክት አፈፃፀም ላይ በተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ለተገኙ ግኝቶች/ግድፈቶች/ የማሻሻያ ሀሳብ የተሰጡ በመሆኑ እነዚህን ግኝቶች ለማሻሻል ኢኒስቲትዩቱ የድርጊት መርሃ ግብር አዘጋጅቶ በወቅቱ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ያልላከ ሲሆን በክትትሉ ኦዲቱ ወቅት ለኦዲት ቡድኑ ሊቀርብ ያልቻለ በመሆኑየተሰጡ የማሻሻያ ሀሳቦች መተግበራቸውንና ችግሮቹ መቀረፋቸውን መሰረት በማድረግ ነው፡፡

15. የክትትል ኦዲቱ በዋነኛነት የተከናወነው በቆላ ዝንብና የገንዲ በሽታ መቆጣጠሪያና ማጥፊያ ኢኒስቲቲዩት ዋና መ/ቤት ቃሊቲ ፣በናሙና በተመረጡ የኢኒስቲትዩቱ የቃሊቲ የቆላ ዝንብ ማራቢያና ማምከኛ ማዕከል፣ የአርባምንጭ የቆላ ዝንብ ገንዲ በሽታ መቆጣጠሪያና ማጥፊያ ማዕከል እና የዲላ ጣቢያ ቅርንጫፍ መ/ቤት በመገኘት ለሚመለከታቸው ሠራተኞችና የሥራ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ፣ ከኢኒስቲትዩቱ የቆላ ዝንብና የገንዲ በሽታ አፈጻጸም ጋር ተያያዥ የሆኑ መረጃዎችን በመከለስ፣በመስክ ምልከታ በከብቶች ጀርባ ኬሚካል የሚቀባበትን በረት፣የከብቶች የኬሚካል አቀባብ ፣ እና መጋዘኖችን በአካል በመገኘትና በመመልከት ኦዲቱ ያስገኘውን ጥቅም በመገምገምነው፡፡

## የክትትል ኦዲቱመመዘኛ መስፈርቶች (Standards of follow up Audit)

16. የክትትል ኦዲቱ የመመዘኛ መስፈርቶች ቀደም ሲልበ2003/2004 ዓ.ም የደቡብ ኢትዮጵያ ስምጥ ሸለቆ የቆላ ዝንብ ማጥፊያ ፕሮጀክት አፈፃፀምላይ በተከናወነው የክዋኔ ኦዲት በተገኙ ግኝቶች/ግድፈቶችን ለማስተካከል የተሰጡ የማሻሻያ ሃሳቦች (Audit recommendation) መሰረት በማድረግ ኢኒስቲትዩቱ ባዘጋጀው የድርጊት መርሃ ግብር የመጡ ለውጦችን ማየት እናችግሮች ያልተሻሻሉ (ያልተቀረፉ) ከሆኑ ምክንያቶቹን በመመርመር የክዋኔ ኦዲቱ ያስገኘውን ውጤት መፈተሽ ነው፡፡ የማሻሻያ ሀሳቡ በአባሪ 1 ላይ ተመልክቷል፡፡

# ክፍል ሁለት

## በክትትል ኦዲት ወቅት የተገኙ የኦዲት ግኝቶች

**ኢኒስቲትዩቱ በእቅዱ መሰረት(ከ1990 ዓ.ም እስከ 2000 ዓ.ም) ውስጥ በደቡብ ኢትዮጵያ ስምጥ ሸለቆ የቆላ ዝንብን ከ 25,000 ካ.ኪ.ሜ ላይ ነፃ ማድረግን በተመለከተ፡-**

17. ኢኒስቲትዩቱ በእቅዱ መሰረት (ከ 1990 ዓ.ም እስከ 2000 ዓ.ም) ውስጥ በደቡብ ኢትዮጵያ ስምጥ ሸለቆየቆላ ዝንብን ከ25,000 ካ.ኪ.ሜ ላይ ነፃ ሊያደርግ ይገባል፡፡
18. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው ፤
    - ✓ የደቡብ ኢትዮጵያ ስምጥ ሸለቆ የቆላ ዝንብ ማጥፊያ ፕሮጀክት በተያዘለት የዕቅድጊዜ (ከ1990 ዓ.ምእስከ 2000 ዓ.ም) ውስጥ የቆላ ዝንብን ከ25,000 ካ.ኪ.ሜላይነፃማድረግያለበትቢሆንምከ13 ዓመታትበኋላየተሰራውበ6,000 ካ.ኪ.ሜላይብቻመሆኑንከ2003 ዓ.ምየዕቅድአፈፃፀምሪፖርትላይለማወቅተችሏል፡፡
    - ✓ በኦዲቱ በመስክ ጉብኝት ወቅት በጣቢያዎች በመዘዋወር ከባለሙያዎች ጋር በተደረገው ቃለምልልስ በወላይታ ሶዶና በዲላ የፕሮጀክቱ ጣቢያዎች የቆላ ዝንብና የገንዲ በሽታ ከመቀነስ ባሻገር ነፃ የሆነ አካባቢ አለመኖሩና እንዲሁም በአርባምንጭ ነፃየ ሆነ አካባቢ ያለ ቢሆንም የዝንቡ መጠን ካልቀነሰበት ቦታ ለሚፈልሱ ዝንቦች መከላከያ /Barrier/ ተሰርቶ የመቆጣጠር ስራ ባለመሠራቱ ከቆላ ዝንብ ነፃ ሆኖአል ለማለት የማያስችል መሆኑ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡
    - ✓ የፕሮጀክቱየጣቢያኃላፊዎችይህንኑበማስመልከትተጠይቀውበሰጡትመልስ፤ የወላይታሶዶኃላፊየቆላዝንብናየገንዲበሽታከመቀነስባሻገርነፃየሆነአካባቢአለመ ኖሩን፣የዲላ ጣቢያ ኃላፊ የኬሚካልና የታርጌት አቅርቦት በበቂ መጠን ስለማይኖር ፣ከቆላ ዝንብና ከገንዲ በሽታ ነፃ የሆነ አካባቢ አለ ለማለት የሚያስቸግር መሆኑን የገለፁ ሲሆን፣የአርባ ምንጭ ኃላፊ ነፃ የሆነ ብዙ አካባቢ ቢኖርም ባሪየር/ቁጥጥር/ ተደርጎ መከላከያ እስካልተደረገ ድረስ

ዝንብ እየገባ ሊወጣ ስለሚችል በትክክለኛነት መግለጽ እንደሚያስቸግር ገልፀዋል፡፡

- ✓ እንዲሁም ስለሁኔታው የፕሮጀክቱ ኃላፊዎች በሰጡት ምላሽ ከ1990 ዓ.ም. እስከ 2003 ዓ.ምበ6,880 ካ.ኪ.ሜ የሚሸፍን አካባቢ ከ90-95% ከቆላ ዝንብ የመቀነስ ስራ የተሰራ መሆኑን እና ይህ ሊሆን የቻለው አንዳንድ እስከ አሁን እየተጠቀሙባቸው ባለው ቴክኖሎጂ የማይደርስባቸው አካባቢዎች የቆላ ዝንብ መሸሸጊያ በመሆን የተቀነሰባቸውን አካባቢ እንደገና በመውረርና በመበከላቸው የተነሳ ሲሆን፤እነዚህም አካባቢዎች ፓርኮች፣ጥብቅ ደኖች፣ሰውና እንስሳት የሌሉባቸው፣ለተሽከርካሪና ለእግረኛ የማያስገቡ አስቸጋሪ አካባቢዎች በመኖራቸው ምክንያት መሆኑን እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት ደግሞ ከ25,000 ካ.ኪ.ሜ ላይ 18,000ካ.ኪ.ሜ ላይ የቅነሳ ሥራው የተጠናቀቀ መሆኑን ገልፀዋል፡፡
- ✓ የ3ቱም ጣቢያዎች ኃላፊዎች እቅዱ ከአፈጻጸሙ ያነሰበትን ምክንያትን ሲገልፁ፣ የሰው ኃይል እጥረት፣ የኬሚካል እና የታርጌት አቅርቦት ማነስ፣ የሌሎች ማቴሪያል አለመሟላት እና የመሳሰሉት እንደሆኑ ከቀረበላቸው መጠይቅ እና ከመረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡
- ✓ በተመሳሳይ ሁኔታ የደቡብ ክልል ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ኃላፊ የፕሮጀክቱ አፈጻጸም ስለዘገየበት ምክንያት ተጠይቀው በሰጡት ፤ ምላሽ ከዚህ ቀደም ህብረተሰቡን የባለቤትነት ስሜት ፈጥሮ አለመንቀሳቀሱ፣ የግብዓት አቅርቦት አናሳ መሆን፣ የተያዘው 25,000 ካ.ኪ.ሜ የቆዳ ስፋት ወጣ ገባና ለሥራ በጣም አመቺ አለመሆኑ ከግምት ውስጥ አለማስገባት፣ በፓርኮች ላይ የቅነሳ ስራ አለመሰራቱ እና የተጠቀሙበት ቴክኖሎጂ ውስን/ታርጌትና በከብቶች ላይ ኬሚካል መቀባት ብቻ/ በመሆናቸው ነው በማለት ገልፀዋል፡፡ ነገር ግን በመጀመሪያም እቅዱ ሲታቀድ ይህንኑ የቦታ አቀማመጥ ከግምት ውስጥ በማስገባት ስለሆነ የተሰጡትን ምክንያቶች መቀበል አልተቻለም፡፡
- ✓ በኦዲቱ ወቅት ፕሮጀክቱ ባለፉት አስርት አመታት ጊዜ ውስጥ አላማውን ከግቡ እንዳይመታ ካደረጉት ነገሮች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ፤ ጠንካራ የማኔጅመንት ክትትል ወቅቱን ጠብቆ አለመከናወን፣ በስራ(በትግበራ ወቅት) የሚያጋጥሙ ችግሮች በግልፅ አለመገለጻቸው፣ የኬሚካሎችና

የታርጌቶች/በኬሚካል ተነክሮ ለዝንቦች መከላከያ በዛፍ ላይ የሚሰቀል ጨርቅ/ ግዢ ከውጪ ሀገር ስለሚከናወን የግዢዎች መዘግየት፣ የሰው ኃይል እጥረት(የባለሙያ)፣ የማቴሪያሎች አለመሟላት በመሳሰሉት ምክንያቶች በተያዘለት እቅድ ጊዜ ግቡን እንዳይመታ ማድረጉን ከዓመታዊ ሪፖርቶች ለማወቅ ተችሏል፡፡

- ✓ በመሆኑም ባለፉት 10 ዓመታት ጊዜ ውስጥ የተሰሩ ስራዎች በጣም አናሳ(በእቅድ ከተያዘው ያነሰ) ቢሆንም በ2003 ዓ.ም እና በ2004 ዓ.ም እንቅስቃሴው ከበፊቱ የሚሻል ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በኦዲቱ ወቅት በጣቢያዎች ጉብኝት በተደረገበት ወቅት በህዳርና ታህሳስ ወር 2004 ዓ.ም አካባቢ ኬሚካሎችና ታርጌቶች በብዛት በመግባታቸው ምክንያት በወላይታ ሶዶ ሁምቦ ወረዳ አባላ ፋራቶ ቀበሌ ገበሬ ማህበር፣ አርባምንጭ ዙሪያ ወረዳ፣ በሁምቦ ወረዳ ዘይሴ ወዘቃ ቀበሌ እና አባያ ወረዳ ዱቢቻ ቀበሌ በዛ ያሉ ከብቶች 1% ( አንድ ፐርሰንት) ዴልታሜትሪን ለማስረጨት አርሶአደሮች ከብቶቻቸውን ይዘው አምጥተው ስራውም /ርጭቱም/ በተግባር ሲከናወን ተመልክቷል፡፡ ነገር ግን በርጭቱ ወቅት አንዳንድ አርሶአደሮችን በመጠየቅ ለመረዳት እንደተቻለው የኬሚካል እርጭቱ በመከናወኑ በጣም ተጠቃሚ እንደሚያደርጋቸው፣ የርጭት ተግባሩ በአብዛኛው የሚካሄደው በ3 እና በ4 ወር አካባቢ መሆኑ፣ የኬሚካል እርጭቱ በተካሄደበት ወቅት ዝንቦች እንደሚቀንሱ ኬሚካሉ ሲጠፋ ዝንቦቹ ተመልሰው ስለሚመጡ የርጭት ተግባሩ በተከታታይ ቢያንስ በየ2 ወሩ ቢደረግ እና ዝንቦች በጣም በሚበዙበት ወቅት /ከሚያዝያ-ነሐሴ/ በየወሩ እርጭቱ ቢከናወን የሚል አስተያየት አክለው ገልፀዋል፡፡
- ✓ በኬሚካል የተነከሩ ጨርቆች /ታርጌቶች/ አንዴ ተተክለው ለ1 ዓመት ያህል ኬሚካሉ ሳይጠፋ አገልግሎት መስጠት እንደሚችሉና በ2004 ዓ.ም ኬሚካሎችና ታርጌቶች በመግባታቸው ምክንያት እንስሳት በማይገቡበት አካባቢ ታርጌቶች እየተተከሉ መሆኑን ከጣቢያ ኃላፊዎች የተገለፀልን ሲሆን፤ ነገር ግን አንዳንድ አርሶአደሮች የተተከሉ ታርጌቶችን ነቅለው በመውሰድ ችግሩ እንዳይቀረፍ በማድረግ ላይ እንደሚገኙ በመስክ

ጉብኝት በተደረገበት ወቅት ከአርባ ምንጭ የፕጀክቱ ጣቢያ ኃላፊ ጋር በተደረገ ውይይት ለማወቅ ተችሏል፡፡

19. ኢኒስቲትዩቱ በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተሰጠውን ማሻሻያ ሃሳብ ተግባራዊ ያደረገ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

- በደቡብ ኢትዮጵያ ስምጥ ሸለቆ ውስጥ ከሚገኙ ሁለት የቆላ ዝንብ ዝርያዎች ግሎሲና ፓሊዲፐስ እና ግሎሲና ፋስኪፐስ ውስጥ ግሎሲና ፓሊዲፐስ በእንስሳት ላይ በርካታ የገንዲ በሽታን የሚያስተላልፍ ሲሆን ግሎሲና ፋስኪፐስ ግን በግጦሽ ቦታ ላይ ስለማይገኝ በእንስሳት ላይ የሚያስከትለው የገንዲ በሽታ መጠነኛ ሆኖ እያለ በብዛት እየተራባ ና እየመከነ ወደ መስክ እየተለቀቀ ያለው ይኸው የቆላ ዝንብ ዝርያ በመሆኑና ምንም እንኳ የግሎሲና ፓሊዲፐስ ቁጥር በተወሰነ ደረጃ እድገት እያሳየ መጥቷል ቢባልም ከአዝጋሚ አዙሪት ያልወጣ መሆኑን እናበወንዞች አካባቢ የቆላ ዝንብ አለመቀነስ እንዲሁም የመሬት ለመሬት ርጭት የተጠናከቀረ አለመሆኑን የሳይንስና፣መገናኛና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የደቡብ ኢትዬጵያ ስምጥ ሸለቆ የቆላ ዝንብ ማጥፊያ ፕሮጀክት የመስክ ምልከታ ባደረገበት ወቅት ከተፃፈ ሪፖርት ለማወቅ ተችሏል፡፡
- የደቡብ ክልል ማዕከል ኃላፊ ከፃፉት የኢትዮጵያ የመካነ ነፍሳት (SIT) ቴክኖሎጂ አጠቃቀምና ችግሮቹ ጥናታዊ ጽሁፍ ለመረዳት እንደተቻለው በደቡብ ኢትዩጵያ ስምጥ ሸለቆ የቆላ ዝንብ ማጥፊያ ኘሮጀክት አማካይነት ከ1990 ዓ/ም ጀምሮ እንቅስቃሴ የተጀመረ ቢሆንም እስከ 2007 ዓ/ም አጋማሽ ድረስ 1000 ካ.ኪ.ሜ በማይሞላ የደሚ ሸለቆ ላይ ከሚደረግ የሙከራ ስራ ያለፈ መሬት ላይ የታየ ተጨባጭ ውጤት የሌለ በመሆኑ፣ አገሪቷ ከ240,000 ካ.ኪ.ሜ ውስጥ 25,000 ካ.ኪ.ሜ ላይ የቆላ ዝንብን ነፃ ሊያደርግ የሚችል ተጨማሪ ከፍተኛ ሀብት እንደሚያስፈልግ ገልፀዋል፡፡

20. የዲላ ጣቢያ ሀላፊ ስለ ጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት መልስ፤ይሄን ያህል ስኳር ኪሎ ሜትር ከቆላ ዝንብ ነፃ ነው ለማለት እንደሚያስቸግር፣ በጊዜያዊነት አከባቢው ከቆላ ዝንብ ነፃ ሊሆን እንደሚችል ነገር ግን ተመልሶ ነፃ የሆነው አከባቢ እንደሚወረር ገልፀዋል፡፡

21.የአርባምንጭ ማዕከል ኃላፊ በበኩላቸው በደቡብ ኢትዮጵያ 30,000 ካሬ ኪሎ ሜትር ከቆላ ዝንብ የፀዳአከባቢ መኖሩን የፀዳ ሲባል ግን ሙሉ ለሙሉ ሳይሆን ከ 90 እስከ 95 ፐርሰንት መሆኑን፣ ከቆላ ዝንብ የፀዳ መሆኑን የሚታወቀውም ትራፕ/ወጥመድ/ በመጠቀም በትራፕ በተያዘው ዝንብ በመሞርከዝ ነፃ መሆኑን እንደሚታወቅ፣ በትራፑ ምንም የቆላ ዝንብ ካልተያዘ አከባቢው ከቆላ ዝንብ የፀዳ መሆኑን እንደሚያረጋግጡ ገልፀዋል፡፡

22.በመሆኑምበደቡብኢትዮጵያ ስምጥ ሸለቆ የቆላ ዝንብ ማጥፊያ ፕሮጀክት ከ1990 ዓ/ም ጀምሮ እንቅስቃሴ የተጀመረ ቢሆንም እስከ 2008 ዓ/ም ኢጋማሽ ድረስ ምን ያህል ካ.ኪ.ሜ ከቆላ ዝንብ እንደፀዳ የማይታወቅ መሆኑን፣ አገሪቷ ከ240,000 ካ.ኪ.ሜ ውስጥ 25,000 ካ.ኪ.ሜ ላይ የቆላ ዝንብን ነፃ ሊያደርግ የሚችል ተጨማሪ ከፍተኛ ሀብት እንደሚያስፈልግ ያሳያል፡፡

## በኢኒስቲትዩቱ በየዓመቱ የሚዘጋጁ እቅድና የእቅድ አፈፃፀምን በተመለከተ ፡-

23.ኢንስቲትዩቱ ግቡን ለማሳካት የሚያስችሉ ዕቅዶች በየዓመቱ ሊያዘጋጅ እና በዓመታዊ ዕቅድ የተያዙ ስራዎች ስለመሰራታቸው ክትትልና ግምገማ ሊያደርግ ይገባል፡፡

24.በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው ፤

- ✓ በ2002 ዓ.ም እና በ2003 ዓ.ም እንስሳት በማይገቡበት አካባቢ መሬት ለመሬትና የአውሮፕላን ላይየኬሚካል እርጭት ለማከናወን በዕቅድ ቢያዝም፤ እስከ የካቲት 2004 ዓ.ም ድረስ ያልተከናወኑ መሆኑን በመስክጉብኝት ወቅት ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ነገር ግን በመጋቢት ወር 2004 ዓ.ም የመሬት ለመሬት የኬሚካል እርጭት ተግባር የተጀመረ መሆኑን በዋና ዳይሬክተሩ ቃለ-መጠይቅ ወቅት ተገልጾልናል፡፡

በተጨማሪም በ2002 ዓ.ም 240,000 የመከኑ ወንድ የቆላ ዝንቦችን መስክ ለመልቀቅ ዕቅድ የተያዘ ቢሆንም፤ እስከ የካቲት 2004 ዓ.ም ድረስ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ሆኖም የእርባታ ክፍሉ ጉብኝት በተደረገበት ወቅት ከመጋቢት 2004 ዓ.ም ጀምሮ የመከኑ ወንድ የቆላ ዝንቦችን መስክ ለመልቀቅ በዝግጅት ላይ እንደሆኑ የክፍሉ ቡድን መሪ ያብራሩ ሲሆን በኦዲቱ የመስክ ጉብኝት ወቅት በካርቶን ለመልቀቅ የተዘጋጁትን ወንድ የቆላ ዝንቦች የታዩና በሚያዝያ 2004 ዓ.ም 158,405 የመከኑ የፋስኪፐስ ወንድ የቆላ ዝንቦች መለቀቃቸው ከሚያዝያ 2004 ዓ.ም ወርሃዊ ሪፖርት ላይ ለማወቅ ተችሏል፡፡

25. ኢኒስቲትዩቱ በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተሰጠው የማሻሻያ ሃሳብ ተግባራዊ የተደረገ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

- ኢኒስቲዩቱ የኬሚካል እርጭት ፕሮግራሙን ለህብረተሰቡ ቀድሞ የማያሳወቅ መሆኑን የሳይንስና፣መገናኛና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የደቡብ ኢትዬጵያ ስምጥ ሸለቆ የቆላ ዝንብ ማጥፊያ ፕሮጀክት የመስክ ምልከታ ባደረገበት ወቅት ከተፃፈ ሪፖርት ለማወቅ ተችሏል፡፡
- በቆላ ዝንብ ማርባት እና ማምከን ላይ 55 % የተሰራ መሆኑን በአጠቃላይ እቅዱ በብሄራዊ ፅ/ቤት 50 % መሆኑን፣ የክትትልና የመረጃ አያያዝ ችግሮች መኖራቸውን፣የተላኩት የዝንብ ቁጥሮች አሳሳች መሆኑን፣ እቅዶቹ በሚፈለገው መልኩ በጥራት አለመፈፀማቸውን፣ የግብረ መልስ አሰጣጥና የመረጃ አያያዝ ክፍተቶች መኖራቸውን፣ በአሮፕላን ሊለቀቁ የቀረቡትን የመከኑ ወንድ ዝንቦች በወቅቱ ሊሰራጭ አለመቻሉን ከስራ አመራር ስብሰባ ቃለ-ጉባኤ ለማወቅ ተችሏል፡፡
- በኢኒስቲትዩቱ ያሉ መረጃዎች እንደሚያሳዩትየውጤት ተኮር እቅድ ክንውን አፈጻጸም ግምገማን በሚመለከት በሁሉም የስራ ሂደት ወጥ የሆነ መረጃ በተደራጀ መልኩ መያዝ ላይ ክፍተት መኖሩን፣በጥቅል ግዥ ለመግዛት ዕቅድ ውስጥ ያልተካተቱ ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ አስቸኳይ ግዥዎች መኖራቸው ታውቋል፡፡

- ከኢኒስቲትዩቱ የ2008 በጀት ዓመት የውጤት ተኮር እቅድ ቃሊቲ በሚገኘው የቆላ ዝንብ ማራቢያና ማምከኛ ማዕከል የግሎሲና ፋስኪፐስ የቆላ ዝንቦችን ቁጥር 750,000 ለማድረስ ታቅዶ 27,8000 በማድረስ የእቅዱ 37.1% መከናወኑን እንዲሁም ቃሊቲ በሚገኘው የቆላ ዝንብ ማራቢያና ማምከኛ ማዕከል የሚመረቱ ወንድ የቆላ ዝንቦችን በጋማ ጨረር አምክኖ በአይሮፕላን መስክ የመልቀቅ ስራ 224,000 ግሎሲና ፓሊዲፐስ የቆላ ዝንቦችን ለመልቀቅ ታቅዶ የእቅዱ 50%መከናወኑ ፣ በእንስሳት ጀርባ የሚቀባው ኬሚካል (DELTHAMETRIN 1 %) ሁሉንም እንስሳት ሙሉ ለሙሉ ያለማዳረስ እና ወቅቱን ጠብቆ የማይሰራ መሆኑን፣ ኬሚካል በእንስሳት ጀርባ የመቀባት ስራ በተያዘለት እቅድና ፕሮግራም ሳይቆራረጥ ሙሉ ለሙሉ አለመተግበሩን ፣ ኬሚካል የተነከሩ ታርጌቶች በስፋት ሁሉንም ቦታዎች ያልሸፈኑ መሆኑን፣ የታቀዱና ፕሮግራም የተያዘላቸው ትግባራት አለመፈፀማቸውን፣ ታውቋል፡፡
- ስራዎች በእቅዱ መሰረት መሰራቱን የመከታተል፣ድጋፍ የመስጠትና የማረም እጥረቶች መኖራቸውን፣ እቅዱን በቁርጠኝነት የመፈፀም ድክመት በአንዳንድ ሰራተኞች መታየቱን ከ2006 ዓ.ም የውጤት ተኮር እቅድና ምዘና ስርዓት ግንባታ ሰነድ ለማወቅ ተችሏል፡፡

26. ከዲላ ጣቢያ የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅበ2008 ዓ.ም መሬት ለመሬት እርጭት ያልተካሄደ መሆኑን፣ የአይሮፕላን የኬሚካል እርጭትም በ 2005 ዓ.ም በወላይታ ከተደረገ በኋላ ያልተደረገ መሆኑን፣በዲላ የአይሮፕላን እርጭት ተደርጎ የማያውቅ መሆኑን፣እንዲሁም በዲላ ጣቢያ የመከኑ የቆላ ዝንቦች ተለቀው እንደማያውቁ፣ አርብቶ አደሩም የአይሮፕላኑን እርጭት በተደጋጋሚ እንደሚጠይቃቸውእና የአይሮፕላን እርጭት ውጤታማ እንደሚያደርግ እንዲሁም በ 2007 ዓ.ም 4000 የቆላ ዝንብ ኬሚካል የተነከሩ ታርጌቶችን ለመትከል እቅድ ተይዞ 620 ታርጌት በመትከል አፈፃፀሙ 15.5% መሆኑን እና አፈፃፀሙም ዝቅ ሊል የቻለው ለታርጌት መንከሪያ የሚያገለግለው 20 % ዴልታሜትሪን ኬሚካል እጥረት የተነሳ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

27.ኢኒስቲትዩቱ ከፕሮጀክት ወደ ኢኒስቲትዩትነት ተቀይሮ በአዲስ መልክ ስራ በሚጀምሩበት ወቅት ከ2005-2007 ዓ.ም ያለምንም ዓይነት እቅድና የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርት እንዳላገኙ የፕላንና ፕሮግራም ዳይሬክተር በኦዲት ቡድኑ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ለማወቅ ተችሏል፡፡

28.በመሆኑን ኢንስቲትዩቱአመታዊ እቅድ አውጥቶየመምራትና ሥራን የመመዘን፣ የክትትል፣ የግብረመልስ አሰጣጥ እና የመረጃ አያያዝ ክፍተቶች በመኖራቸው ግልጽ፣ ወጥ የሆነና የማይጣረዝ መረጃ ለማግኘት እና ጥንካሬና ድክመትን በጊዜ ለይቶ የእርምት እርምጃ እንዳይወስድ አድርጎታል፡፡

## ኢኒስቲትዩቱ የተያዘለት በጀትአጠቃቀም እና ለኢኒስቲትዩቱ የሚያስፈልጉ መሳሪያዎችና መድኃኒቶች ግዥን በተመለከተ ፡-

29.ኢኒስቲቲዩቱ ከመንግሥት የሚመደብለትን በጀት የመፈጸምና የመጠቀም አቅም ሊያጎለብት ይገባል፡፡ኢኒስቲትዩቱ ለዕርባታ ማዕከሉና ለመስክ ስራ የሚያገለግሉ መሳሪያዎች፣ መድኃኒቶች እና ኬሚካሎች ግዢ በተያዘላቸው እቅድ መሠረት ሊከናወኑ ይገባል፡፡

30.በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው ፤

- ✓ ለፕሮጀክቱ ከ1990 እስከ 2003 ዓ.ም. ድረስ ባሉት 13 ዓመታት ውስጥ ለፕሮጀክቱ ከመንግስት የተመደበ በጀት ብር 129,518,497 ፤ ከዚህ ውስጥ ሥራ ላይ የዋለው ብር 72,674,931 ሲሆን ፤ ብር 56,843,566 ወይም 43% ያህል ያልተጠቀሙበት በጀት ሆኖ ተገኝቷል፡፡
- ✓ የበጀት አስተዳደርን በተመለከተ በሩብ አመቱ በጥቅል አነስተኛ በጀት አፈጻጸም መታየቱ በፕሮጀክቱ ጽ/ቤት ከጠቅላላ በጀት በሩብ አመት አፈጻጸሙ 22% በታች መሆኑ፣
- ✓ በፕሮጀክቱ የግዢ ሂደታቸው ከተጀመረ ሁለት አመት እና ከዚያ በላይ የሆናቸው የግዢ ሂደቶች፣ ለላቦራቶ የሚያስፈልጉ ግዢዎች ከተጠየቁ ስድስት ወር ያለፉቸው እና ለመስክ አገልግሎት ሊውሉ የሚችሉ ማቴሪያሎች የግዢ ጥያቄ ቀርቦ ነገር ግን ግዢያቸው ያልተፈፀሙ

እንዳሉ ለማወቅ ተችሏል እንደዚሁም የቆላ ዝንቦች ማምከኛ እና ደምን ከባክቴሪያ ለማፅዳት የሚያገለግል ጨረር(Industrial radiateor Gama ray) ግዢ የተፈፀመና ነገር ግን ለኢንዱስትሪያል ራዲያተር የሚያስፈልገው ክፍል ግንባታ ያልተሰራ በመሆኑ ዕቃው ያልገባ መሆኑን በተጨማሪ ለማወቅ ተችሏል፡፡

- ✓ የኢንዱስትሪያል ራዲያተር ግዢ የተጠናቀቀ ቢሆንም እስካሁን ሥራ ላይ ባለመዋሉ ምክንያት ያስከተለው ተፅዕኖ መኖሩን የእርባታ ማዕከሉ ኃላፊና ቡድን መሪዎች ባንድ ላይ በሰጡት ምላሽ፤ እስካሁን በመዘግየቱ ምክንያት የቆሙ ስራዎች ባይኖሩም ወደፊት የዝንቦች ቁጥር በሚጨምርበት ጊዜ የደም ማጥሪያ ሊያንስ ስለሚችል የዝንቦች እርባታ ቁጥሩ እንዳያድግ እንደሚያደርግና መሳሪያው ተገዝቶ በቅርቡ እንደሚመጣ በመጥቀስ ሲመጣ የሰራተኞችን የስራ ጫና እንደሚቀንስ፣ ጊዜ እንደሚቆጥብ፣ ብዙ ደም ራዲየት (Radiate) እንደሚደረግ፣ ስራዎች በዘመናዊና በፈጣን ሁኔታ ስለሚሰሩ የዝንቡ ቁጥር በፍጥነት ጨምሮ ከታሰበው ግብ ለመድረስ እንደሚቻልና በተጨማሪም ላለው አንድ የጨረር መሳሪያ ጫና እንዲቀንስና ከብልሽት መቀነስ ሊረዳ እንደሚችል ገልፀዋል፡፡
- ✓ ይሁን እንጂ እስከ 2002 ዓ.ም መጠናቀቅ የነበረባቸው ግዢዎች እንደ ማጠቢያ ማሽኖች፤ ዳይክሶንመደርደሪያዎች፤ ከቆሻሻ ነፃ ማድረጊያ ማሽኖች (Sterilizing Ovens) የመመገቢያ ትሪ ማጠቢያ (Tray Washing Machines)፤ ኦፕልኬተር (የኬሚካል መቀቢያዎች)፣ ሬጀንቶች፤ ማይክሮስኮፖችና ሴንትሪፌውጅ የመሳሰሉት/ እና ለላቦራቶሪ ክፍል በጣም አስፈላጊ የሆኑ እንደ/ሴንሴቲቭ ባላንስ፣ ፔትሪድሽ፣ ዲስታል፣ ኦቨን፣ ቴርሞ ሜትር፤አፕልኬተር፤ ኬሚካል እና ወተርባዝ የመሳሰሉት ሊገዙ ከታቀደበት አመት የዘገዩ በመሆናቸው በዕርባታ ክፍሎች እና በላቦራቶሪዎች ስራዎች እቃዎች 16 በመዋዋስ ለአሰራር አመቺ ባልሆነ መልኩ እንዲሰሩ አስገድዷል፡፡ ይህም ለዝንቦች ምግብነት የሚውለውን ደም ብቃት አናሳ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡

31.በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተሰጠው የማሻሻያ ሃሳብ ተግባራዊ የተደረገ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

- በጀትን በተመለከተ ለኢኒስቲቲዩቱ በ 2005 ዓ.ም ከመንግስት የተመደበው በጀት 59,575,381.10 ሲሆን የተጠቀሙበት 58,216,605.03 ፣ ያልተጠቀሙበት ደግሞ 1,358,776.07 ወይም 2.3 ፐርሰንት መሆኑን፤ በ 2006 ዓ.ም ከመንግስት የተመደበው በጀት 49,362,572,.11 ሲሆን የተጠቀሙበት 34,499,727.81፣ያልተጠቀሙበት ደግሞ 14,862,844.30 ወይም 43 ፐርሰንት መሆኑን፤ እንዲሁም በ 2007 ዓ.ም ከመንግስት የተመደበው በጀት 47,556,473,.71 ሲሆን የተጠቀሙበት 39,094,308.42 ፣ ያልተጠቀሙበት ደግሞ 8,462,165.29 ወይም 21 ፐርሰንት መሆኑን ከፋይናንስ ከተገኘ ምንጭ ለመረዳት ተችሏል፡፡
- ከ2006 በጀት ዓመት የጥቅምት ወር የለውጥ ዕቅድ አፈጻጸም የበጀት አስተዳደርን በተመለከተ በሩብ አመቱ በጥቅል አነስተኛ በጀት አፈጻጸም መታየቱ በፕሮጀክቱ ጽ/ቤት ከጠቅላላ በጀት በሩብ አመት አፈጻጸሙ 22% በታች መሆኑ፣በአንዳንድ የበጀት አርእስቶች አነስተኛ የበጀት አፈጻጸም መታየቱን፣በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የሁለተኛ በጀት ዓመት የበጀት አፈጻጸሙ አብዛኛው 50% በታች መሆኑ አነስተኛ አፈጻጸም በመሆኑና በአሁኑ ደረጃ የሚቀጥል ከሆነ ከፍተኛ የበጀት ብክነት ስለሚደርስ ከወዲሁ ሥራው ትኩረት ተሰጥቶበት ከእቅድ ጋር እየተገናዘበ እንዲሰራ ያስገነዘቡ ስለመሆኑ ለመስክ ሥራ የተላኩ የሥራ ማስኬጃ በጀቶችን በየበጀት ርዕሱ ተጠቅሞ በወቅቱ የማወራረድ ድክመት መኖሩን፣ በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ በጀት በተፈለገው ጊዜ መለቀቅ ባለመቻሉ ለሥራ የሚያስፈልጉ ዕቃዎችን በወቅቱ ማሟላት አለመቻሉ፣የመደበኛ በጀት አጠቃቀም ፊዚካል ስራውና በጀኑተ የተጣጣመያለመሆኑ፣ በጀት አጠቃቀሙ አናሳ መሆኑን በኢኒስቲትዩቱ የሁለተኛ በጀት ዓመት የበጀት አፈጻጸሙ አብዛኛው 50% በታች መሆኑ አነስተኛ አፈጻጸም በመሆኑና በአሁኑ ደረጃ የሚቀጥል ከሆነ ከፍተኛ የበጀት ብክነት ስለሚደርስ ከወዲሁ ሥራው ትኩረት ተሰጥቶበት ከእቅድ ጋር እየተገናዘበ መሰራት እንዳለበት ለመረዳት ተችሏል፡፡

- የበጀት አስተዳደርን በተመለከተ በሩብ አመቱ በጥቅል አነስተኛ በጀት አፈጻጸም መታየቱ፣ እንዲሁም በኢኒስቲትዩቱ ከጠቅላላ በጀት በሩብ አመት አፈጻጸሙ 22% በታችመሆኑን ከ2006 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ አመት የኦዲት ምርመራ ውጤት ለማወቅ ተችሏል፡

32.ከዲላ ጣቢያ የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ የበጀት አጠቃቀም ችግር የሚፈጠረው በጀቱ ሲመጣላቸው ዘግይቶ መሆኑን በዚህም ምክንያት በጀቱን ሳይጠቀሙ እንደሚቀሩ፣ የበጀት እጥረትም እንዳለባቸው እና ከ ሀምሌ እስከ ህዳር 2008 ዓ.ም ድረስ በጀት ያልነበራቸው መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

33.ከአርባምንጭ ማዕከል የስራ ኃላፊ ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ እንደተቻለው በጀት የሚፈቀድላቸው በኢኒስቲትዩቱ መሆኑን፣ ከዚያም የሚያስፈልጋቸውን በየወሩ እንደሚላክላቸው፣ ዓመታዊ የሚመደብላቸውን በጀት እንደማያውቁት ገልፀዋል፡፡

34.ለግዢ፤ ለሥራ ማስኪያጃና ለመሳሰሉት ተግባራት መዋል ከሚገባው የኢኒስቲቲዩቱ አመታዊ በጀት አብዛኛው ሥራ ላይ አለመዋሉ ኢኒስቲቲዩቱ ካለመው ግብ እንዳይደርስ ያደረገው መሆኑ እና ለታየው አዝጋሚ ለውጥ መንስኤ መሆኑ እንዲሁምማዕከላት የተመደበላቸውን በጀት ባለማወቃቸውና በአንድ ጊዜ ባለመሰጠቱአመጣጥነው መስራት ያለባቸውን ስራ እንዳይሰሩ እና የሚያስፈልጋቸውን ግዢ በወቅቱ እንዳያከውኑ አድርጓል፡፡

35.ኢኒስቲዩቱ ለመስክ አገልግሎት የሚውልዴልታሜትሪን 1% ብዛት 20,000 ሊትር በነጠላ ዋጋ 408 ብር በጠቅላላ ዋጋ 8,160,000 ብር፣ ዴልታሜትሪን 20% ደግሞ ብዛት 2,500 ሊትር በነጠላ ዋጋ 2,567.88 ብር በጠቅላላ ዋጋ 6,419,700 ብር በአጠቃላይ የሁለቱ ድምር 14,579,700 ብር ኬሚካል ለመግዛት የመንግስት ግዢና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ሳያውቅ ጨረታ መውጣቱን፣ ከአሸናፊው ድርጅት ከ ከጄኔራል ኬሚካልስ ኤንድ ትሬዲንግ ኃ.የተ.የግ.ማ ጋር ጥር 2/2006 ዓ.ም የ14,579,700 የግዢ የውል ስምምነት መደረጉን፣ ኬሚካሉን አቅራቢ ድርጅት ለጨረታው ማስከበሪያ 10% ብር 1,457,970 ለኢኒስቲትዩቱ ማስያዝ ቢኖርበትም ያላስያዘ መሆኑን፣ ኬሚካል አቅራቢው ድርጅቱ ከጠቅላላ የውል ስምምነቱ ውስጥ ዴልታሜትሪን 1% ብዛት 8,877 ሊትር፣ በብር የ 3,621,816 ኬሚካል ብቻ አቅርቦ ክፍያው የተፈፀመለት መሆኑን፣ በውሉ ስምምነት መሰረት ጄኔራል ኬሚካልስ ኤንድ

ትሬዲንግ ኃ.የተ.የግ.ማ ውሉን በማፍረሱ የ14,579,700 ብር አስር ፐርሰንት 1,457,970 ብር መቀጣት ቢኖርበትም ኢኒስቲትዩቱ ምንም ዓይነት እርምጃ ያልወሰደ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይህ ሆኖ ሳለ ኢኒስቲትዩቱ እንደገና በ 2007 ዓ.ም ከጄኔራል ኬሚካልስ ኤንድ ትሬዲንግ ኃ.የተ.የግ.ማ ጋር ዴልታሜትሪን 1% ብዛት 64,000 ሊትር በነጠላ ዋጋ 12.95 ዶላር በጠቅላላ ዋጋ 828,800 ዶላር፣ ዴልታሜትሪን 20% ደግሞ ብዛት 3,100 ሊትር በነጠላ ዋጋ 43.95 ዶላር በጠቅላላ ዋጋ 136,245 ዶላር በአጠቃላይ የሁለቱ ድምር 965,045,488 ዶላር የኬሚካል ግዢ ስምምነት ማድረጉን በተጨማሪም በ 2008 ዓ.ም ከጄኔራል ኬሚካልስ ኤንድ ትሬዲንግ ኃ.የተ.የግ.ማ ጋር ዴልታሜትሪን 1% ብዛት 75,000 ሊትር በነጠላ ዋጋ 12.70 ዶላር በጠቅላላ ዋጋ 952,500 ዶላር፣ ዴልታሜትሪን 20% ደግሞ ብዛት 3,500 ሊትር በነጠላ ዋጋ 43.90 ዶላር በጠቅላላ ዋጋ 153,650 ዶላር በአጠቃላይ የሁለቱ ድምር 1,144,488 ዶላር የኬሚካል ግዢ ስምምነት ማድረጉን ከግዢ የውል ስምምነት ለማወቅ ተችሏል

36. ለቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቁጥጥር የሚውል 20% እና 1% ዴልታሜትሪን ኬሚካል በሀገር ውስጥ አለመገኘት፣ የውጭ የግዥው ሂደት ግዜ በመውሰዱ ሥራ ላይ ጫና ማሳደሩን፣ በሚፈለገው ጊዜ ለግዢ ክፍያ ገንዘብ አለመለቀቅ በዚህም ምክንያት ግብአቶች በወቅቱ አለመቅረባቸውን፣ የቆላ ዝንብን ለመቀነስ ጥቅም ላይ የሚውል የታርጌት ግዥ መዘግየትና በዚህ የተነሳ የመስክ ሥራን በወቅቱ መስራት አለመቻሉን፣ ኢኒስቲትዩቱ የቆላ ዝንብና የገንዲ በሽታ ለመቀነስና ለማጥፋት ለሚጠቀማቸው የተለያዩግ ግብዓቶች ማለትም የኬሚካል፣ታርጌት፣ወዘተ ግዢዎች በወቅቱ አለመከናወንና ተገልጋዩና ተጠቃሚው ህብረተሰብ ዘንድ አለመድረሱን ከ2008 በጀት ዓመት የውጤት ተኮር እቅድ ለመረዳት ተችሏል፡፡

37. በበደሌንኡስማዕከልየታርጌትጨርቅ ግዥ አሸናፊ ድርጅት የሆነው ኮምቦልቻ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ላይ ማቅረብ አለመቻሉን በመግለጹ ያለው የበጀት ጊዜም አጭር በመሆኑ ጨርቁ ሳይገዛ መቅረቱን ለማወቅ ተችሏል፡፡

38. ከዲላ ጣቢያ የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ ለመስክ አገልግሎት የሚያገለግሉ መሳሪያዎች ግዢ እንደሚዘገዩ እንዲሁም ጥራታቸውን ያልጠበቁ እንደሚሆኑ፣ የታርጌት፣ የዴልታሜትሪን 1% እና 20% ፣ የቲባር አፕሊኬተር እጥረት እንዳለባቸው ለመረዳት ተችሏል፡፡

39.የግዢ ፍላጎታቸውን ለኢኒስቲትዩቱ እንደሚያቀርቡ፣ በማዕከል ግዢ መፈፀም እንደማይችሉ በዚህም ምክንያት ግዢዎች በእቅዱ መሰረት እንደማይከናወኑ እንዲሁም አንዳንድ ኬሚካሎች የማይገዙበት ጌዜም እንዳለ ከአርባምንጭ ማዕከል የስራ ኃላፊ ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ ለመረዳት ተችሏል፡፡

40. ኢኒስቲትዩቱ በውጭ ምንዛሪ የሚገዛቸው የተለያዩ ግብዓቶች ማለትም የኬሚካል፣ የታርጌት፣ወዘተ ግዢዎች በቅድሚያ ለበጀት ዓመቱ የሚያስፈልገው ግብዓት ታቅዶ ከማለቁ በፊት ተከታታይ የግዢ ትዕዛዝ ባለመሰጠቱ፣ አቅራቢ ድርጅቶች በገቡት የግዢ ውል መሠረት ማቅረባቸውን ክትትልና ቁጥጥር ባለማድረጉና እንዲሁም በማዕከል ግዢ መፈፀም ባለመቻሉ በሚፈጠረው ሂደት ሥራው በታቀደው መሠረት እንዳይከናወን አድርጓል፡፡

## በኢኒስቲትዩቱ የንብረት አያያዝ ፣አወጋገድ እና ተገዝተው ያለአገልግሎት የተቀመጡ ንብረቶችን በተመለከተ፡-

41.በኢኒስቲትዩቱ በመንግስት የንብረት አስተዳደር መመሪያ መሠረት ወጥ የሆነ የተጠናከረ የንብረት አያያዝ ሊኖር ይገባል፡፡ጥቅም ላይ ሊውሉ የማይችሉትን የመንግሥት ንብረቶች በወቅቱ የመንግሥት ንብረት አወጋገድ ሥርዓትን ተከትሎ ሊያስወግድ ይገባል፡፡ተገዝተው ለታቀደላቸው ዓላማ ሳይውሉ ያለአገልግሎት የተቀመጡ ንብረቶች አገልግሎት ላይ ሊውሉ ይገባል፡፡

42.በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፣

- ✓ በኦዲቱ ወቅት ለማየት እንደተቻለው በኘሮጀክት ማዕከሉ የንብረት ክፍል(መጋዘን)ውስጥየተለያዩዕቃዎች/በካርቶን የተቀመጡ ማይክሮስኮፖች፣ የታርጌት ጨርቆች …/ በተዘበራረቀ ሁኔታና ዕቃ ለማውጣት በማይመች መልኩ መሬት ላይ ተቀምጠው መታየታቸው፣ አንዳንድ ዕቃዎች ሳይለዩ በካርቶን እንደታሸጉ ለብዙ ጊዜ ያለአገልግሎት መቀመጣቸው፣ በመስክ ጣቢያዎችም በንብረት ክፍል ጥበት ምክንያት ንብረቶች በተጨናነቀ ሁኔታ መቀመጣቸው፣ ኬሚካሎችና የተለያዩ መድኃኒቶች ከተለያዩ ንብረቶች ጋር ተቀላቅለው መቀመጣቸው፤ በተለይ በዲላ ኬሚካሎች ከነ ካርቶናቸው

በቢሮ ውስጥ የተቀመጡ ሲሆን፣ በተጨማሪ ንብረቶች በውጪ/በኮርደር/ ላይ ተቀምጠው ታይተዋል፡፡

- ✓ እንዲሁም ወረዳዎች ኬሚካሎችን ከጣቢያዎች በሚረከቡበት ጊዜ በሞዴል 22 ወጪ ተደርጐ ቢረከቡም፤ ወረዳዎች በሞዴል 19 ገቢ እና በሞዴል 22 ወጪ እንደማያደርጉና ተከታታይ ቁጥር በሌላቸው ቅጾች ገቢ እና ወጪ እንደማያደርጉ ታውቋል፡፡
- ✓ ይህን በማስመልከት የደቡብ ክልል ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፤ በዲላ የፕጀክቱ ጣቢያ የመጋዘን ችግር እንዳለ ጠቁመው ነገር ግን ይህ ችግር ሊፈጠር የቻለው ለስራ የተከራዩት ቤት የቀበሌ በመሆኑ መጋዘን ለመስራት ጠይው ስላልተፈቀደላቸው በየሰራተኞች ቢሮ እንዲሁም ውጪ /በቨረንዳ/ ላይ እቃዎችን ለማስቀመጥ እንደተገደዱ ገልጸዋል፡፡
- ✓ የኘሮጀክት ማዕከሉ ዋና ዳይሬክተር ስለዚህ ጉዳይ በሰጡት ምላሽ፤ የማዕከሉን የንብረት አያያዝ በተመለከተ ጽ/ቤቱ የንብረት ማስቀመጫ የሚሆን መደርደሪያ በውጭ ሀገር የግዢ ሂደት ላይ የሚገኝና ተገዝቶ ሲገባ ችግሩ እንደሚፈታ እምነታቸው እንደሆነና እስከዚያ ግን ያሉትን ዕቃዎች በየጊዜው ጥብቅ ክትትል እየተደረገላቸው እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡የጣቢያዎችን ንብረት ክፍል(መጋዘን) በማስመልከት ኘሮጀክቱ በየጣቢያዎች የራሱ የሆኑ ጽ/ቤቶች የሌለውና ግማሹ በትብብር የተገኙ መሆናቸውንና የዲላ ጣቢያ ግን ከቀበሌ ላይ በኪራይ የተያዘና በውስጡም መለስተኛ መጋዘን ለመስራት 18 ቀበሌው ባለመፍቀዱ ችግሩ ከሌሎች ጣቢያዎች ጎላ ብሎ እንዲታይ ማድረጉን ገልጸዋል፡፡
- ✓ በተጨማሪም ወረዳዎች ከጣቢያዎች ኬሚካል በሞዴል 19 እንደማይረከቡና የሚረከቡት ኘሮጀክቱ ባዘጋጃቸው በተዋረድ በተለያዩ ቅጾች አማካኝነት እንደሆነ እና ይህ የተደረገው መድሐኒቱ ለህብረተሰቡ በነጻ አገልግሎት ስለሚሰጥና የተቀላጠፈና ፈጣን አገልግሎት ለመስጠት ታስቦና የተለያዩ አካላትም ኃላፊነት እንዲወስዱ ታስቦ የተዘጋጀ እንደሚመስላቸውና ይህም የተዘጋጀው

ከዚህ ቀደም በነበሩት አመራር ሲሆን፤ አዲስ የገቡትም ከዚህ ቀደም የነበረውን አሰራር ተከትለው እየሰሩና እስከአሁን ድረስ ምንም የአሰራር ግድፈት ያልታየበትና ሁሉም ባለድርሻ አካላት ቁጥጥር ሊያደርጉበት የሚችል የአሰራር ስልት እንደሆነም ለማወቅ እንደቻሉ ገልፀዋል፡፡

- ✓ ይሁን እንጂ በፕሮጀክት ማዕከሉ ንብረት ክፍል ንብረቶች በተዘበራረቀ ሁኔታ መሬት ላይ መቀመጣቸውና በቢን ካርድ ተመዝግበው አለመያዛቸው ከውጪ የሚመጡ ንብረቶች አይነታቸው ተለይቶ ለአገልግሎት ሳይውሉ እንዲቆዩ፣ እቃዎችን በመፈለግ የስራ መጓታት ማስከተል፣ ንብረቶችን ለብልሽት እንዲዳረጉ እና ንብረት ክፍሉ እንዲጣበብ ያደርጋል፡፡
- ✓ በኦዲቱ ወቅት በ3ቱም ጣቢያዎች አገልግሎት ላይ የዋሉ የኬሚካል ዕቃዎች አወጋገድ ወጥ የሆነ መመሪያ የሌለ መሆኑ፣ ጣቢያዎች እቃዎቹ አርብቶአደሩ ለሌላ አገልግሎት እንዳያውላቸው በማለት ቆራርጠው እንደሚያቃጥሏቸውና ወጥ የሆነ መመሪያ ያልደረሳቸው መሆኑ፣ በቆላ ዝንብ አካባቢ የሚኖሩ በስራው ላይ ተሳታፊ የሆኑ ብቃት ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎችን ለመምረጥ የሚያገለግል ወጥ የሆነ የመምረጫ መስፈርት የሌለና ጣቢያዎች በራሳቸው ባስቀመጡት መስፈርት የሚመርጡ መሆኑ፤ ተበላሽተው ሁለት ዓመታትና ከዚያ በላይ የሆናቸው ሁለት መኪኖች እና አምስት ሞተር ብስክሌቶች ካለአገልግሎት ተቀምጠው መገኘታቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡
- ✓ የኬሚካል ዕቃዎች አወጋገድን በተመለከተ የመስክ ኦፕሬሽን ዳይሬክተሩ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፤ መመሪያ ተዘጋጅቶ ለህትመት መቅረቡንና ስለአወጋገዱም ስልጠና ተሰጥቶ እና ውይይት ተደርጎ መመሪያው ለሁሉም መሰጠቱን በፅሁፍ የገለፁ ቢሆንም መረጃው ሊቀርብልን አልቻለም፡፡
- ✓ ዋና ዳይሬክተሩ ስለሁኔታው በሰጡት ምላሽ፤ የመንግስት የግዢ መመሪያ፣ የሊጋሽ አካላት የግዢ መመሪያ እና ያገለገሉ ዕቃዎች

አወጋገድ መመሪያ በማዕከሉ መኖሩን የገለፁ ቢሆንም፤ የንብረት አስተዳደርን መመሪያ መረጃ በተመለከተ የቀረበ ሲሆን ነገር ግን በመመሪያው መሰረት እንደማይሰራ እና የኬሚካል ዕቃ አወጋገድ መመሪያ በተመለከተ መረጃ አልቀረበም፡፡

- ✓ ሆኖም አገልግሎት ሰጥተው ወይም በተለያዩ መንገዶች የተበላሹና አገልግሎት ላይ ሊውሉ የማይችሉ ዕቃዎችን አወጋገድ በንብረት አስተዳደር መመሪያ ላይ ያለ ቢሆንም፤ በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በንብረት ክፍል እና በእርባታ ማዕከሉ አገልግሎት መስጠት ያቆሙ የልብስ ማጠቢያዎች፣ ማይክሮስኮፖችና በጣቢያዎችም አገልግሎት መስጠት ያቆሙ ሞተር ሳይክሎች መኖራቸው፤ በተጨማሪም በወላይታ ሶዶ ለረጅም ጊዜ በመጋዘን የተቀመጠ ጥቁር የትራኘ ጨርቅ መኖሩ፣ አገልግሎት ሰጥተው ወይም በተለያዩ መንገዶች 20 የተበላሹና አገልግሎት ላይ ሊውሉ የማይችሉ ዕቃዎች በ2004 ዓ.ም የ6 ወር ሪፖርት አፈጻጸም ላይ መኖራቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይሁን እንጂ ተጠግነተው ስራ ላይ እንዲውሉ ወይም ተጠግነው አገልግሎት መስጠት ካልቻሉ የሚወገዱበት መንገድ ሳይመቻች የተቀመጡ መሆኑ የታወቀ ሲሆን፤ ይህንን ለማድረግ በዓመታዊ እቅድ እና በስትራቴጂክ እቅድ ላይ ተኩረት ተሰጥቶት በዕቅድ የተያዘ አለመሆኑ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይህም በጣቢያዎች ንብረት ክፍል ጥበት የተነሳ ዕቃዎች በመጨናነቅ ስለሚቀመጡ ጉዳት ሊደርስባቸው ስለሚችል ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡
- ✓ በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ንብረት ክፍል/መጋዘን/ እና በእርባታ ክፍል ውስጥ ተገዝተው አገልግሎት ሳይሰጡ አምስት አመት እና ከዚያ በላይ የሆናቸው አምስት ኦቨኖች፣ ሁለት የሙቀት መቆጣጠሪያ መሳሪያዎች(cold room)፣ አምስት ማይሮስኮፖች፣ አንድ የትሪ ማጠቢያ ማሽን (Sterilizer)፣ አንድ የውሃ ማጠራቀሚያ ታንከር እና የመሳሰሉት አገልግሎት ሳይሰጡ ለረጅም ጊዜ መቆየታቸውን ለመረዳት ተችሏል፡፡

- ✓ በንብረት ክፍሉ ውስጥ የሚገኙ እነዚህ ንብረቶች በተለያዩ የስራ ክፍሎች እና በፕሮጀክቱ ጣቢያዎች የሚፈለጉ ሲሆን፣ ነገር ግን እነዚህን እቃዎች ጠይቀው ለተለያዩ የስራ 24 ክፍሎች ሳይሟሉ ለረጅም ጊዜ የቆዩ መሆናቸውን እና በንብረት ክፍል እያሉ ለስራ ክፍሎች አለመሰራጨታቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡
- ✓ ሌላው የስራው ፀባይ ከሚያስፈልገው ነገሮች ውስጥ አንዱ የውሃ አቅርቦት ሆኖ ሳለ ለውሃ ማጠራቀሚያ አገልግሎት ተብሎ ከተገዛ አንድ ዓመት ያስቆጠረ የውሃ ማጠራቀሚያ በመውጫ ስብሰባ ወቅት አገልግሎት እንዲሰጥ ተደርጓል ቢባልም ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ አገልግሎት ላይ ሳይውል ተቀምጦ ተገኝቷል፡፡ ለዝንቦች እርባታ አገልግሎት የሚውለው Humidifier /የክፍሉን ሙቀት መቆጣጠሪያ/ውሃ ከሌለ ችግር የሚፈጥር መሆኑ፣ የዝንቦች መመገቢያና የመሳሰሉት ንፅህና ካልተጠበቀ በዝንቦች እርባታ ላይ ችግር ማስከተሉ፣ በኦዲቱ ወቅት አገልግሎት እየሰጠ የሚገኘው የውሃ ማጠራቀሚያ ታንከር ከተገጠመ ብዙ ዓመት የሆነውና የዛገ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡ የውሃ ማጠራቀሚያው ስራ ላይ አለመዋል ውሃ በጠፋ/በተቋረጠ/ ጊዜ ችግሩን የከፋ የሚያደርገውና በሚረቡ ዝንቦች ላይ ከንፅህና ጉድለትም ሆነ ከክፍሉ ሙቀት መቆጣጠሪያ የተነሳ የሞት አደጋ ሊፈጥር የሚችል መሆኑ ሊታወቅ ይገባል፡፡
- ✓ የዕርባታ ማዕከል ውስጥ የሚገኘውን የትሪ ማጠቢያ የዕርባታ ማዕከሉን በጐበኘንበት ወቅት ከሚመለከታቸው ሠራተኞች ገለጻ እንደተረዳነው ተገዝቶ አገልግሎት የማይሰጥበት ምክንያት በግልፅ ባይታወቅም እንዴት አገልግሎት እንደሚሰጥ ባለመታወቁ ምክንያት እና ተበላሽተው አገልግሎት መስጠት ያቆሙትን በተመለከተ ዕቃዎቹ ከውጪ በመምጣታቸው ስለአጠቃቀሙ የሚያውቅ የባለሞያ አለመኖር ምክንያት መሆኑን ለማወቅ ችለናል፡፡
- ✓ የፕሮጀክት ኃላፊዎች በሠጡት ምላሽ ዕቃዎቹ በቅርቡ /በ2004/ ከውጭ የገቡ በመሆናቸው ርክክባቸው ያላለቀ መሆኑን እና

የተረከቧቸው ዕቃዎችን ደግሞ የሚገጥም ባለሙያ ለማግኘት በጨረታ ሂደት ላይ እንደሚገኙና ቀሪዎቹ በቅርብ ጊዜ ስራ እንደሚጀምሩ የገለፁ ሲሆን በመውጫ ስብሰባ ወቅት የውሃ ሮቶን በተመለከተ ተገጥሞ ስራ ላይ እንደዋለ አስረድተዋል፡፡

- ✓ የጽ/ቤቱ ሃላፊ ይህንን ይበሉ እንጂ በወላይታ ሶዶ፣ በአርባ ምንጭ እና በዲላ ጣቢያ የሚገኙ የፕሮጀክቶቹ ጣቢያ ኃላፊዎች የማይክሮስኮፕ እጥረት እንዳለ መግለጻቸው፤ በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ለዝንቦች እርባታ /Insectory/ ክፍል የሚያገለግል የዝንቦች መመገቢያ ትሪ ከባክቴሪያ ነፃ ለማድረግ የሚያገለግል የትሪ ማጠቢያ/Tray Washer/ በስራ ክፍሉ እጥረት እንዳለ ነገር ግን እቃው ቢኖርም አጠቃቀሙን የሚያውቅ ሰው ባለመኖሩ ካለአገልግሎት ከስድስት አመት በላይ መቀመጡ፣ የተለያዩ እቃዎች ከባክቴሪያ ነፃ ለማድረግ የሚያገለግሉ ኦቨኖች፣ ዝንቦች የሚመገቡት ደም ከቄራዎች ድርጅት ከመጣ በኋላ ለምግብነት እስከሚዘጋጅ ድረስ አቀዝቅዞ የሚያቆዩ ቀዝቃዛ ክፍሎች(Cold Rooms) ስራ ያልጀመሩ መሆናቸውና ለላብራቶሪ ክፍል የሚረዱ መሳሪያዎች በንብረት ክፍሉ ውስጥ እያሉ የእቃው አይነት በንብረት ክፍል ባለሞያ ባለመታወቁ አገልግሎት ሳይሰጡ መቀመጣቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡ በመሆኑም ከላይ የጠቀስናቸው ማቴሪያሎች በቅርብ የገቡ ሳይሆን ከተገዙ ሁለት ዓመትና ከዚያ በላይየሆናቸው ሲሆኑ በቅርቡ የገቡ አዳዲስ ማቴሪያሎችም እንዳሉ ታውቋል፡፡ በመሆኑም የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ኃላፊ የሰጡትን መልስ ለመቀበል ያዳግታል፡፡ምክንያት መሆኑን ለማወቅ ችለናል፡፡

43.በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተሰጠው የማሻሻያ ሃሳብ ተግባራዊ የተደረገ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

- በኢኒስቲትዩቱ ካሉ መረጃዎች ለመረዳት እንደተቻለው አገልግሎት ላይ ሊውሉ የሚችሉ ንብረቶች በንብረት ክፍል መከማቸታቸው / በተለይም ለመስክ አገልግሎት የሚውሉ ንብረቶች/፣ ለቋሚ እቃዎች የመለያ ቁጥር አለመሰጠቱ፣ የኢኒስቲትዩቱ ያገለገሉ ንብረቶች አያያዝና አወጋገድ ለብልሽትና ለብክነት የተጋለጠ መሆኑን ፤
- የኢኒስቲትዩቱ ያገለገሉ ንብረቶች አያያዝና አወጋገድ ለብልሽትና ለብክነት የተጋለጠ መሆኑን እንዲሁም ኬሚካልና መድሀኒቶች የመጡባቸው ቁሳቁሶች አወጋገድ ችግር መኖሩን፤
- በኢኒስቲዩቱ መጋዘን ውስጥ ያሉ ንብረቶች መካከል አብዛኛዎቹ ዋጋቸው ያልተገለፀ መሆኑን ኢኒስቱትዩቱያሉትንንብረቶችከመዘገበበት ዝርዝር ማስረጃ ለመመልከት ተችሏል፡፡
- ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ ንብረቶችን ጠግኖ በስራ ላይ እንዲውል አለማድረግ ወይም ህግና መመሪያ በሚያዘው መሰረት በወቅቱ አለማስወገድ ፣ በእቃ ማከማቻ መጋዘኖች የቦታ ጥበት በመፍጠር ለአላስፈላጊ የመጋዘን ኪራይና ወጪ ሊዳርግ መቻሉን፤
- በኢኒስቲትዩቱ መጋዘን ውስጥ በ2006 ዓ.ም ገቢ የሆኑና የሚጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፈባቸው54,885 (ሀምሳ አራት ሺህ ስምንት መቶ ሰማንያ አምስት)አልፋሚዲየም /ALFAMYDIUM/ ኬሚካል በንብረት ክፍል በካርቶን እንደታሸገ መኖሩን የኦዲት ቡድኑ መጋዘኖቹን በሚመለከትበት ጊዜ ለማየት መቻሉ እንዲሁም በምልከታው ወቅት እነዚህ መድሀኒቶች ወደ አርባምንጭ ጣቢያ ሊላኩ በሂደት ላይ መሆናቸውን ለመመልከት ተትሏል፡፡

44.በዲላ ጣቢያ መጋዘን ውስጥ ያሉ የተለያዩ ኬሚካሎች፣ አላቂ እቃዎች እና ቋሚ እቃዎች መካከል አብዛኛዎቹ ላይ ቢን ካርድ የሌለ መሆኑን ፣በመጋዘን ውስጥ እቃዎች እርስ በርስ ተፋፍገው እና ተደራርበው መቀመጣቸውን ፣ የእቃ መደርደሪያ የሌለ መሆኑ እንዲሁም የእቃ ማስቀመጫው መጋዘን ጠባብ መሆኑን፣ መጋዘኑ በመጋዘኑ ካሉት እቃዎች ገር የማይመጣጠን መሆኑን፤ መጋዘኑ የጠበበ

በመሆኑ እቃዎች በረንዳ ላይ እና ግቢ ውስጥ ተከምረው የተቀመጡ መሆኑን እንዲሁም ለዝናብና ለፀሀይ የተጋለጡ መሆናቸውን  የኦዲት ቡድኑ ለመመልከት ችሏል፡፡



*ሥዕል1፡- በዲላ መጋዘን ኬሚካል የተነከሩ ጨርቆችና ሌሎች ንብረቶች የተቀመጡበት ሁኔታ*

45.ስለጉዳዩ የኢኒስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ተጠይቀው በሰጡት መልስ በዲላ ጣቢያ መጋዘንንብረቶች ላይ ቢን ካርድ አለ ብለዋል፡፡

46. ይሁን እንጂ የኦዲት ቡድኑ በዲላ ጣቢያ ተገኝቶ መጋዘኖችን በጎበኘበት ወቅት አብዛኛዋቹ ንብረቶች ላይ ቢን ካርድ የሌለ መሆኑን፣ እንዲሁም የተወሰኑ ንብረቶችም ላይ የሚገኘው ቢን ካርድ እቃዎቹ ገቢ እና ወጪ መደረጋቸውን በትክክል የማያሳይ መሆኑን የኦዲት ቡድኑ ለመመልከት ችሏል፡፡

47.በአርባምንጭ መጋዘን ውስጥ ያሉ የተለያዩ ኬሚካሎች፣ አላቂ እቃዎች እና ቋሚ እቃዎች ላይ ቢን ካርድ የሌለ መሆኑን ፣ እቃዎች እርስ በርስ ተፋፍገው እና ተደራርበው መቀመጣቸውን የኦዲት ቡድኑ ለመመልከት ችሏል፡፡

48.በዲላ ጣቢያ በመጋዘኑ ውስጥ በበረንዳ እና በግቢ ውስጥ አገልግሎት የማይሰጡ 11 የመስክ ወንበሮች፣ 7 ድንኳኖች፣ 6 የመስክ አልጋዎች፣ 137 የተበላሹ ኬሚካል መርጫዎች፣23 የኒሳን ፒክ አፕ እና 44 የፎርድና የኒሳን ፓትሮል ጎማዎች፣ 13

ከመነዳሪ፣ 1 የሞተር ሳይክል ባትሪ፣ 14 ፊልትሮ፣ 3 የኒሳን ፓትሮል ዳፕራተር፣ 8 አሞርዛተር፣ 1 ዲስክ፣ የፍሪሲዮን ሸራ፣ 1 የሞተር ጥርስ፣ 1 የፎርድ ካርትሽ፣ 6 ኮቺኔት፣ 1 ቴስቲኒ፣ 1 ሆርን፣ 2 ቺንጋ፣ 1 የመኪና ሸራ፣ 1 ሞቶሮላ የሬዲዮ መገናኛ፣ 2 የሰሌዳ ቁጥራቸው 4-4339 እና 4-4337 የሆኑ ሞተር ሳይክሎች መኖራቸውን የኦዲት ቡድኑ ለመመልከት ችሏል፡፡ ስለ ጉዳዩ የዲላ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው ጥቅም ላይ ሊውሉ የማይችሉ የመንግስት ንብረቶች ተወግደው እንደማያውቁ እና አሁን ለማስወገድ ለአስወጋጅ ኮሚቴ ለመስጠት የሚወገዱ ንብረቶችን ማዘጋጀታቸውን ለመረዳት ተችሏል፡፡



*ሥዕል 2፡- በዲላ የመጋዘን ጥበት በመኖሩ ንብረቶች በረንዳ ላይ ተቀምጠው*

49.በአርባምንጭ ማዕከል መጋዘን ውስጥ አገልግሎት የማይሰጡ 2 የኮምፒተር ባትሪ፣ 4 አዳፕተር፣10 ማከፋፈያ፣ 1 ተሽከርካሪ ወንበር፣ 2 የመኪና የፊት መስታወት፣ 23 የማይሰራ ቻርጄብል ባትሪ ፣2 የስልክ ቀፎ፣ 1 የላፕቶፕ ቦርሳ፣ 2 የማይሰራ ሳምሶናይት፣ 1 ኮምፒውተር፣ 1 የተበላሸ ፎቶ ኮፒ ማሽን፣ 3 ዴል ላፕቶፕ፣ 1 ፕሪንተር ፣1 ታይፕ ራይተር፣1 ፋይል ካቢኔት፣1 የመስክ ወንበር፣3 ፓወር ሰፕላይ፣ 1ትንሽ ፕሪንተር፣ 1 ትልቁ ዋሪት ፍሪጅ፣ የአገልግሎት ዘመናቸው ያለፈ /expired/ ያደረጉ 14,000 ቫክትነር /vacutainer/ የደም ናሙና መውሰጃ ከነመርፌው

መኖራቸውን የኦዲት ቡድኑ ለመመልከት ችሏል፡፡ ስለጉዳዩ የአርባምንጭ ማዕከል የስራ ኃላፊ ተጠይቀው ጥቅም ላይ ለውሉ የማይችሉትን የመንግስት ንብረቶች ማስወገድን በተመለከተ የእነሱ ድርሻ የሚወገዱ ንብረቶችን ለይተው ለኢኒስቲትዩቱ ማሳወቅ እንጂ ማስወገድ እንደማይችሉ ነገር ግን ማዕከሉ ሀዋሳ እያለ ህዳር 2008 ዓ.ም ንብረቶች የተወገዱ መሆናቸውን ለመረዳት ተችሏል፡፡

50.በኢኒስቲትዩቱ መጋዘን ውስጥ በ 05/09/2006 ዓ.ም ገቢ የሆኑና ያለአገልግሎት የተቀመጡ አራት አዳዲስ ሊፋን ሞተር ሳይክሎች ያለአገልግሎት መቀመጣቸውን ፣ 5000 ሊትር የሚይዝ የውሃ ማጠራቀሚያ ታንከር ያለአገልግሎት መቀመጡን፣ በ05/09/2006 ዓ.ም ገቢ የሆኑ ብዛታቸው 58 የሆኑ የመስክ ፍራሾች ያለአገልግሎት መቀመጣቸውን፣ በ 2006 ዓ.ም የገቡ ብዛት ያላቸው የተለያዩ ለቆላ ዝንብ የማጥፋት አገልግሎት የሚውሉ ኬሚካሎች እንዲሁም እቃዎች መኖራቸውንና ቁጥረቸውም ከ2006 ዓ.ም ጀምሮ ያልቀነሰ መሆኑን /ወጪ ያልተደረጉ/ መሆናቸውን የኦዲት ቡድኑ መጋዘኖቹን በሚመለከትበት ወቅት ለመመልከት ተችሏል፡፡

51.በዲላ ጣቢያ በመጋዘኑ ውስጥ የተበላሸ እና ጥገና የሚያስፈልገው አንድ ጀነሬተር፣ የተበላሸ እና ጥገና የሚያስፈልገው አንድ ማይክሮስኮፕ፣ አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ነገር ግን በመጋዘን የተቀመጡ አምስት ሞተር ሳይክሎች ያለአገልግሎት መቀመጣቸውን እንዲሁም በግዢ ትዕዛዝ ስህተት /ስፔሲፊኬሽን/ ችግር ምክንያት ተገዝተው ያለ አገልግሎት የተቀመጡ መሳሪያዎች መኖራቸውን፣ ዳይመንድ ፔንስል የማይክሮስኮፕ ስላይድ መቅረጫ አዘው የመጣላቸው እርሳስ መሆኑን፣ ሪቻርጄብል ባትሪ ጠይቀው ያለ ስፔሲፊኬሽን መጥቶ እጃቸው ላይ የፈነዳባቸው መሆኑን ፣ በዚህም ምክንያት ያለአገልግሎት መቀመጡን ለማወቅ ተችሏል፡፡

52.በአርባምንጭ የቀድሞ የማዕከሉ የቆላ ዝንብ እርባታ ክፍል /insectory / ውስጥ ያሉ ለቆላ ዝንብ እርባታ የሚያገለግሉ ትላልቅ እና ውድ መሳሪያዎች ሁሉም ሙሉ ለሙሉ ያለአገልግሎት መቀመጣቸውን፣ መጠኑ ትልቅ የሆነ ጀነሬተር ያለአገልግሎት መቀመጡን፣ መጠኑ ትልቅ የሆነ ማቀዝቀዣ ያለአገልግሎት መቀመጡን፣ የኦዲት ቡድኑ ለመመልከት ችሏል፡፡



*ሥዕል3 ፡- በአርባምንጭ ማዕከል ያለአገልግሎት የተቀመጠ የቀድሞ የቆላ ዝንብ ማራቢያ ክፍል*



*ሥዕል4፡- በአርባምንጭ ማዕከል ያለአገልግሎት የተቀመጠ ጀነሬተር*

53. በኢኒስቲትዩቱ በእርባታ ማዕከሉ ንብረት ክፍል/መጋዘን/ ውስጥ አገልግሎት ሳይሰጡ እንደታሸጉ የተቀመጡ 5 ኦቨኖች፣ 2 የሙቀት መቆጣጠሪያ መሳሪያዎች/ cold room/፣ 5 ማይክሮስኮፖች፣ 4 ሞተር ሳይክሎች፣አንድ የውሀ ማጠራቀሚያ ታንከር፣ ኬሚካል መርጫ መሳርያ / T-bar application /፣ ሴንሴቲቭ ባላንስ፣ ዲስትለር፣ ፔትሪዲሽ፣ አውቶ ክሌቭ፣ ቴርሞሜትር፣ አልኮል፣ ሲሪንጅ መኖራቸውን ለመመልከት ተችሏል፡፡

54.በኢንስቲትዩቱ የተጠናከረ የንብረት አያያዝ ሥርዓት ባለመኖሩ በቃሊቲ ንብረት ክፍል ለመስክ አገልግሎት ሊውሉ የሚችሉ ንብረቶች እንደ ቲባር አፕሊኬቴርና የመሳሰሉት ተከማችተው ባሉበት ሁኔታ በክልል ባሉ ጣቢያዎች ላይ እጥረት አለ ተብሎ ግዢ መጠየቁ የሥራ አፈጻጸም ላይ ተፅዕኖ አሳድሮዋል፡፡ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ ንብረቶችን ጠግኖ በስራ ላይ እንዲውል አለማድረጉ ወይም ህግና መመሪያ በሚያዘው መሰረት በወቅቱ አለማስወገዱ ፣ በእቃ ማከማቻ መጋዘኖች የቦታ ጥበት በመፍጠር ለአላስፈላጊ የመጋዘን ኪራይ እንዲዳረጉ አድርጓል፡፡በኢኒስቲቲዩቱ ውስጥ በአንድ በኩል አዳዲስ የተገዙ እቃዎችና መሳሪያዎች ለምሳሌ ፡- አራት ሊፋን ሞተር ሳይክሎች፣ ባለ 5000 ሊትር የውሃ ታንከር፣ 58 የመስክ ፍራሾች፣ ለኬሚካል እርጭት የሚያገለግል የኬሚካል መርጫ መሣሪያ T-bar applicator ወዘተ… ገዝቶ አገልግሎት ላይ አለማዋል መታየቱ እና በሌላ በኩል ደግሞ በክልል ጣቢያ ለኬሚካል እርጭት የሚያገለግል የኬሚካል መርጫ መሣሪያ T-bar applicator/ እጥረት መኖር ድርጅቱ በጥናትና ፍላጎት ላይ የተመረኮዘ ግዥ እንደማያካሂድ ያመለክታል፡፡

## በመስክ ስራ ላይ የሚሳተፉ ማህበረሰቦችን መምረጫ መስፈርትን በተመለከተ እና በኢኒስቲትዩቱ ለሚረቡ ዝንቦችም ሆነ ለመስክ አገልግሎት የሚውሉ መሳሪያዎች ስለመሟላታቸው ፡-

55.በኢኒስቱዩቱ በመስክ አገልግሎት ላይ የሚሳተፉ ማህበረሰቦችን መምረጫ መስፈርት/መመሪያ/ ሊኖር ይገባል፡፡በኢኒስቲትዩቱ ለሚረቡ ዝንቦችም ሆነ ለመስክ አገልግሎት የሚውሉ ማቴሪያሎች/ቁሳቁሶች/ ሊሚሉ ይገባል፡፡

56.በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

- ✓ በኦዲቱ ወቅት በቆላ ዝንብ አካባቢ የሚኖሩ በስራው ላይ ተሳታፊ የሆኑ ብቃት ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎችን ለመምረጥ የሚያገለግል ወጥ የሆነ የመምረጫ መስፈርት የሌለና ጣቢያዎች በራሳቸው ባስቀመጡት መስፈርት የሚመርጡ መሆኑን፤
- ✓ በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት በእንስሳት ጀርባ ላይ ኬሚካል የሚቀቡ የማህበረሰቡ አባላትየሚመረጡበት መስፈርት ያለመዘጋጀቱን በተመለከተ የተሰጠ መልስ የለም፡፡

- ✓ በኦዲቱ ወቅት እንደተገነዘብነው በማዕከሉ ለሚረቡ ዝንቦች የሚያገለግሉ ማቴሪያሎች ሳይሟሉ የእርባታ ስራን መጀመር/መስራት/ የማይቻልና የተወሰኑ እንደ ሴንሴቲቭ ባላንስ፣ ዲስትለር፣ፔትሪዲሽ፣አውቶ ክሌቭ፣ ቴርሞሜትር፣ አልኮል የመሳሰሉት እና ለመስክ ስራ የሚያገለግሉም እንደ ማይክሮስኮፕ፣ ኦፕልኬተር /ኬሚካል ለመርጨት የሚያገለግል/ የመሳሰሉትም እጥረት ያለ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡
- ✓ ይህን በማስመልከት የመስክ ኦፕሬሽን ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፤ የኬሚካል መርጫ መሳሪያ እጥረት መኖሩንና በፊት የነበሩትም በመበላሸታቸው የተነሳ በሶዶ ብቻ ሳይሆን በሁሉም ጣቢያዎች ችግሩ በመኖሩ ግዢ ተጠይቆ ከውጭ ሀገር እስከሚመጣ ድረስ እየተጠበቁ እንደሆኑና እስከዚያው በራሱ ኬሚካሉ በሚቀርብበት ፕላስቲክ ላይ መለኪያ ስላለው እንደሚጠቀሙ ገልፀዋል፡፡
- ✓ የፕሮጀክቱ ዋና ዳይሬክተር ደግሞ ስለሁኔታው በሰጡት ምላሽ፤ ለመስክ ስራ የሚያገለግሉ አንዳንድ መሳሪያዎች ለምሳሌ Applicator, Microscope, Centrifuge& Heamatocrit heparinised capillary tube የመሳሰሉት ከዚህ በፊት የነበሩት በእርጅናና በመበላሸት፣ አንዳንዶቹም አላቂ ዕቃዎች በመሆናቸው በአሁኑ ሰዓት እጥረቱ ሊከሰት እንደቻለና ይህንንም ችግር ለመፍታት ከአፍሪካ ልማት ባንክ በተገኘ የብድር ድጋፍ ግዢውን ለመፈጸም አለም አቀፍ ጨረታ ወጥቶ አሸናፊው ድርጅት ሐገር ውስጥ እስከሚያስገባና የጨረታውም ሂደት ረጅም ጊዜ በመውሰዱ በእርግጥ እጥረቱ ሊገጥም የቻለ ቢሆንም ችግሩን ለመፍታት ከአጋር ድርጅቶች ጋር በተለይ ከግብርና ጽ/ቤት ጋር በመቀናጀትና ዕቃዎችን በውሰት በመውሰድ በስራ ላይ ከፍተኛ በደል ሳይደርስ ሥራዎችን ለማከናወን የተቻለ መሆኑንና በአሁኑ ሰዓት ዕቃዎች ከውጭ እየገቡ በመሆኑ ችግሩ ይቃለላል የሚል ግምት እንዳላቸው ገልጸዋል፡፡

- ✓ ሆኖም በኦዲት ወቅት ለመረዳት እንደተቻለው ለእርባታ ማዕከሉ ላብራቶሪ ክፍል የሚያስፈልጉ ምንም እንኳን ስራን እስከማቆም የሚያደርሱ ባይሆኑም ለዝንቦች ምግብነት የሚውለውን ደም ጥራት ለመጠበቅ ከሚያገለግሉ ዕቃዎች ውስጥ ለምሳሌ ቴርሞሜት እና አልኮል የመሳሰሉት እንዳልተሟሉና ለዝንቦች ምግብነት የሚውለውን ደም ከብክነት ነፃ በማድረግ ጥራቱ ካልተጠበቀ ለሚረቡ ዝንቦች የሞት አደጋ አንደኛው ምክንያት እንደሚሆንና እየሆነም እንዳለ፣ ባለ 2 ሊትር ለዝንቦች ምግብነት የሚውለውን ደም ማስቀመጫ ባለመኖሩና ባለ 1 ሊትር በመጠቀማቸው፣ ስሪንጅ ለባለ 2 ሊትር 1 ሲሪንጅ የሚበቃ ቢሆንም ለሁለት ሊትር2 ሲሪንጅ እንዲጠቀሙና የሲሪንጅ ብክነት እንዲኖር23 እንደሚያደርገው ከባለሞያዎቹ ለመረዳት ተችሏል፡፡ በተጨማሪም የዝንቦች ሞት ሲከሰት ናሙና ወስዶ ለመመርመር የሚያስችል ማቴሪያል አለመኖሩና ይህም ችግሩና መንስኤው በወቅቱ እንዳይታወቅ ማድረጉን የ6 ወር ሪፖርት ግምገማ ከሠራተኛና ከባለድርሻ አካላት ጋር ከተደረገ መረጃ ላይ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ለመስክ ስራ ከሚያገለግሉት ውስጥም የማይክሮስኮኘ እጥረት መኖሩ የገንዲ በሽታን ቁጥጥር ለማድረግ ከሚያስፈልጉ ነገሮች ውስጥ አንዱና ዋነኛው በመሆኑ እጥረት መኖሩ የገንዲ ህዋስ የሚገኝበትን ደረጃ ለመገምገም እንዳያስችል እያደረገው ይገኛል፡፡
- ✓ እንደዚሁም የመሳሪያዎች እጥረት ሊከሰት የቻለው ዋነኛው ምክንያት ከአፍሪካ ልማት ባንክ በተገኘ ብድር የሚገዙ ዕቃዎች ግዢ መዘግየት እንደሆነ የቀረበ ቢሆንም፤ በሀገር ውስጥ የሚገዙ የላብራቶሪ ዕቃዎች እንደቴርሞሜትርና አልኮል የመሳሰሉት አለመሟላታቸው ምክንያቱን ተቀባይነት እንዳይኖረው ያደርገዋል፡፡

57. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተሰጠው የማሻሻያ ሃሳብ ተግባራዊ የተደረገ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-
58. በኦዲቱ በመስክ አገልግሎት የሚሳተፉ ማህበረሰቦችን መምረጫ መስፈርት /መመሪያ /የሌለ መሆኑን፣ ህብረተሰቡ በፈቃደኝነት በተራ በተራ በመስክ እንደሚሰማራ ለማወቅ ተችሏል፡፡
59. በከአርባምንጭ ማዕከል በመስክ አገልግሎት የሚሳተፉ ማህበረሰቦችን የመምረጥ ኃላፊነት የማዕከሉ ሳይሆን የቀበሌ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡
60. በመሆኑም የኬሚካል እርጭት እና የታርጌት ተከላ ስራ በጥራት እና በብቃት እንዳይሰራ አድርጓል፡፡
61. በዲላ ጣቢያ ለመስክ አልግሎት የሚውሉ ማቴሪያሎች /ቁሳቁሶች/ ሙሉ ለሙሉ ያልተሟሉ መሆኑን፣ ዴልታሜትሪን 1% እና 20 % እጥረት መኖሩን፣ የታርጌት እጥረት መኖሩን፣ ቲ ባር አፕሊኬተር የሌላቸው መሆኑን ቲ ባር አፕሊኬተር ባለመኖሩም ኬሚካል ከብቶች ላይ በእጅ እየረጩ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል
62. እንዲሁም በአርባምንጭ ማዕከል ለመስክ አገልግሎት የሚውሉ ተሽከርካሪ ችግር እንዳለባቸው፣ያለተሽከርካሪ ስራውን መስራት እንደማይቻል፣ የቲባር አፕልኬተር እጥረት እንዳለባቸው፣ በግዢ መንጓተት ምክንያት መሳሪያዎች እንዳልተሟሉ ከሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡
63. በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ እንደተቻለው ለኬሚካል መርጫ የሚያገለግል የቲባር አፕሊኬሽን አለመሟላትና በዚህ ምክንያት የቅቢ ኬሚካል እየባከነ መሆኑን ፣ መመርመሪያ ኪቶች፣ ሪኤጀንቶችና ኬሚካሎች አለመግባት በኢኒስቲትዩቱ የቆላ ዝንብ ማጥፋት ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ተአኖ አሳድሯል፡፡

## ለቆላ ዝንብ እርባታ የተሰሩ ክፍሎችን /ሞጁልስ/ እናበቆላ ዝንብ አካባቢ የሚኖረው ማህበረሰብና አከባቢ ስላገኘው ጥቅምና ጉዳት ጥናት መደረጉን በተመለከተ ፡-

64.በኢኒስቲትዩቱ ግንባታቸው የተጠናቀቁ ለቆላ ዝንብ ዕርባታ የተሰሩ ክፍሎች /ሞጁልስ/ ስራ ላይ ሊውሉ ይገባል፡፡በቆላ ዝንብ አካባቢ የሚኖረው ማህበረሰብና አካባቢ ከፕሮጀክቱ የተገኘው ጥቅምና ጉዳት ምን ምን እንደሆነ በየሶስት ዓመቱ ጥናት ሊደረግና ሊገመገም ይገባል፡፡

65.በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፣

- ✓ በኦዲቱ ወቅት በፕሮጀክት ማዕከሉ ለቆላ ዝንብ ዕርባታ ከተሰሩት 7 ክፍሎች ውስጥ ስራ የጀመሩትም 2ቱ ብቻመሆናቸው ታውቋል፡፡ ስራ ከጀመሩትም 2ት ክፍሎች አንደኛው ክፍል ማርባት ከሚችለው አቅም በታች እየሰራ እንደሆነ ማለትም ክፍል አንድ(1) ውስጥ የሚረቡ ዝንቦች ቁጥር ከክፍል ሁለት(2) ከሚረቡት በጣም ቁጥራቸው አነስተኛ መሆኑ እና ክፍል አንድ(1) ውስጥ በዛ ያለ መሆናቸውን በእርባታ ማዕከሉ በተጐበኘበት ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡
- ✓ ክፍል ሁለት ውስጥ የሚረቡ ዝንቦች ቁጥር ለምን አነስተኛ እንደሆነ የክፍሉ ቡድን መሪ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፤ በክፍል ሁለት የሚረቡ ዝንቦች ዓይነት ከክፍል አንድ ስለሚለዩ፣ ለማርባት በጣም አስቸጋሪ በመሆኑ፣ በቫይረስ፣ በደምና በተለያየ ምክንያት የሞት አደጋ ስለሚያጋጥማቸው መሆኑን፣ የቫይረስ በሽታን ለመከላከል በደም ውስጥ የሚሰጥ መድኃኒት መጀመራቸውን እና የሞት አደጋን ለመከላከል የሚመገቡትን ደም ጥራት መጠበቅ መሆኑን በጉብኝቱ ወቅት አስተረድተዋል፡፡
- ✓ ስራ ያልጀመሩት ክፍሎች ለምን እንዳልጀመሩ በተመለከተ ደግሞ የእርባታ ማዕከሉ ኃላፊና የክፍሎቹ ቡድን መሪዎች በጋራ የሰጡት ምላሽ የስራው ፀባይ ማቴሪያሎች ሳይሟሉ መስራት ስለማይቻል፣ ለአገልግሎት የሚውሉ መሳሪያዎች ባለመሟላታቸው ምክንያት እና በተጨማሪ ክፍል ሶስትን በቅርብ ለማስጀመር የተገዙ ዕቃዎችም ስራ የጀመሩት ክፍሎች ዕቃ

ሲበላሽ ከዚህ ለማስጀመር ከተገዙ እቃዎች በካሊቬሽን ስለሚወሰድ ክፍሉ /ሞጁሉ/ በቅርቡ ያልተጀመረ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

- ✓ ዋና ዳይሬክተሩም ይህን በማስመልከት የሰጡት ምላሽ ግንባታቸው የተጠናቀቁ አምስት ሞጁልስ ስራ ላይ የሚውሉት የቆላ ዝንቦች ባሉት ሁለት ሞጁሎች ከሞሉ በኋላ በሶስተኛው ውስጥ ዕቃዎች ሲሟሉ ተራ በተራ ስራ ላይ እንደሚውሉ ገልፀዋል፡
- ✓ ይሁን እንጂ በእኛ አስተያየት ለዝንቦች እርባታ የሚያገለግለውን ህንፃ ለመገንባት ብር 16,988,011.86 /አስራ ስድስት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሰማኒያ ስምንት ሺህ አስራአንድ ብርከሰማንያስድስት ሳንቲም/ ከፍተኛ ወጪየወጣበት ሲሆንክፍሎቹ አገልግሎት 27 መስጠት ከሚጠበቅባቸው በታች እያገለገሉ የሚገኙ መሆኑን እና አምስቱ (5) ክፍሎች ሥራሳይጀምሩ ያለአገልግሎት መቀመጣቸው አግባብ ሆኖ አልተገኘም፡፡
- ✓ ፕሮጀክቱ ከጀመረበት ከ1990 ዓ.ም ጀምሮ በ1996 ዓ.ም ብቻ ለህብረተሰቡ ያስገኘውን ጥቅም በተመለከተ ጥናት የተደረገ ሲሆን፤ በመርሃ ግብሩ መሰረት በየሶስት ዓመቱ ያልተገመገመ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡
- ✓ ፕሮጀክቱ እየተተገበረ ባለበት አካባቢ የሚኖሩ ህብረተሰቦች በቆላ ዝንብ መቀነስ ምክንያት ያገኙትን ጥቅም በማስመልከት የ3ቱም ጣቢያ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፤ ማህበረሰቡ የወተትና የስጋ ምርት በመጨመር፣ የእንስሳት ቁጥር በመጨመር፣ ያረገዙ ላሞች ውርጃ በመቀነስ፣ ለገንዲ በሽታ ህክምና ወጪ በመቀነስ፣ የእርሻ በሬ የማረስ አቅም በመጨመር በመሳሰሉት ጥቅም ያገኙ መሆኑን የገለፁ ቢሆንም፤ ይህን ለማወቅ የተቻለው የማህበረሰቡን የዕለት ተዕለት የኑሮውን ለውጥ በመመልከት እንጂ ጥናት ተደርጎ የተገኘ(በጥናት የተደገፈ) አለመሆኑን አስረድተዋል፡፡
- ✓ ዋና ዳይሬክተሩም የሰጡት ምላሽ ፕሮጀክቱ ለህብረተሰቡ ያስገኘው ጥቅም በተመለከተበ1996 ዓ.ም ጥናት የተደረገ ሲሆን ከዚያ ወዲህ ጥናት ያልተደረገ መሆኑን እና አሁንጥናቱን በህብረተሰቡና በተፈጥሮ ሀብት ላይ ማድረጉ አስፈላጊ በመሆኑ ለማከናወን ጥናትየሚያደርጉ ዩኒቨርሲቲዎችን ፕሮጀክቱ እያወዳደረ መሆኑን እና ጥናቱ በቅርብ ቀን ይከናወናል የሚል ግምት መኖሩን ገልጸዋል፡፡ በመቀጠልም ጥናት ማድረጉና በሰነድ

መረጃዎችን መያዙ በቀላሉ ለማስረዳትና ለመግለጽ አስፈላጊ ቢሆንም፤ ዋናው ቁም ነገር ግን በመሬት ላይ ያለው እውነታ የህብረተሰቡ ምስክርነትና እየታየ ያለው ተጨባጭ ለውጥ ኘሮጀክቱ ለሕብረተሰቡ ያስገኘውን ውጤት በበለጠ እንደሚገልጹት ግምታቸውን ገልጸዋል፡፡

- ✓ በኦዲቱ ወቅትም በ3ቱም ጣቢያዎች በተመረጡት ቀበሌዎች በተደረገው ጉብኝት ወቅት አንዳንድ አርሶደሮች ተጠይቀው፤ ኘሮጀክቱ በ2ት ዓመት ውስጥ ለውጥ እንዳመጣላቸውና ከከብቶቻቸውም ሆነ ለም መሬትን አርሶ ከሚያገኙት ምርት ተጠቃሚ እንደሆኑ ለመረዳት የተቻለ ቢሆንም፤ ኘሮጀክቱ በቆላ ዝንብ መቀነስ ምክንያት ለማህበረሰቡ አስገኘ የተባለው ጥቅም በጥናት ተደግፎ ያለመገምገሙ በተለይም 30 ኘሮጀክቱ እስካሁን በህብረተሰቡና በተፈጥሮ ሀብት ላይ ያስከተለው አሉታዊና አዎንታዊ ፋይዳ ተገምግሞ አለመታወቁ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

66.በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተሰጠው የማሻሻያ ሃሳብ ተግባራዊ የተደረገ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

67.በኢኒስቲትዩቱ ግንባታቸው የተጠናቀቁ ለቆላ ዝንብ ዕርባታ የተሰሩ አምስት ክፍሎች/ሞጁልስ/ ስራ ያልጀመሩ መሆኑን፣ አሁን ከ ሰባቱ ክፍሎች ስራ ላይ ያሉት ሁለቱ ብቻ መሆናቸውን፣ ስራ ያልጀመሩት አምስቱ ክፍሎች ስራ ያልጀመሩበት ምክንያት አሁን እጃቸው ላይ ያለው የቆላ ዝንብ ዝርያ ሁለት ብቻ በመሆኑ ይህም በፓይለት/ በጅምር/ ሒደት ላይ በመሆኑ በሁለቱ ዝርያዎች ውጤታማ ከሆኑ ወደ ሌላ አምስት ዝርያዎች እንደሚሸጋገሩ ከሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

68.በመራባት ላይ ያሉት ሁለት ዓይነት የዝንብ ዝርያዎች ውጤቱ ከፖይለት ደረጃ ያላለፈ በመሆኑ16,988,011.86 /አስራ ስድስት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሰማኒያ ስምንት ሺህ አስራ አንድ ብር ከሰማንያ ስድስት ሳንቲም/ብር ከፍተኛ የመንግሥት ሀብት የወጣባቸው የቆላ ዝንብ ማራቢያአምስት ክፍሉች /ሞጁልስ/ ያለአገልግሎት እንዲቀመጡ አድርጓል፡፡

69.በዱላ ጣቢያ በ2005 ዓ.ም የተወካዮች ምክር ቤት የሳይንስና ቴክኖሎጂ ቋሚ ኮሚቴ መጥቶ አንዳንድ አርብቶ አደሮችን ከማነጋገር ውጭ በቆላ ዝንብአከባቢ የሚኖረው ማህበረሰብና አከባቢ ከፕሮጀክቱ የተገኘው ጥቅምና ጉዳት ምን ምን እንደሆነ ጥናቶች ተደርገው እንደማያውቁ ለመረዳት ተችሏል፡፡

70.በቆላ ከአርባምንጭ ማዕከል የስራ ኃላፊ በቆላ ዝንብ አከባቢ የሚኖረው ማህበረሰብና አከባቢ ከፕሮጀክቱ የተገኘው ጥቅምና ጉዳት ምን ምን እንደሆነ በኢኒስቲትዩቱ የተጠና ጥናት አለመኖሩን ነገር ግን የተለያዩ የውጭ ተቋማት ከእነርሱ ጋር በጋራ በመሆን ጥናት ያደረጉ መሆኑን፣በኢኒስቱትዩቱ የተለያዩ አርብቶ አደሮች ጋር እየተዞረ ስላገኙት ጥቅም ቀጥተኛ ያልሆነ ቃለ-መጠይቅ እንደሚደረግ ገልፀዋል፡፡

71.በቆላ ዝንብ አካባቢ የሚኖረው ማህበረሰብ ከፕሮጀክቱ የተገኘው ጥቅምና ጉዳት ምን ምን እንደሆነ በኢኒስቲትዩቱ ጥናት አለመደረጉ ኢኒስቲትዩቱ ያስገኘው ተጨባጭ ለውጥ ምን ምን እንደሆነ እንዳይታወቅ አድርጎታል፡፡

## በእንስሳት ጀርባ ላይ የሚቀባ ኬሚካል መጠን አጠቃቀም ስርዓት ስለመዘርጋቱ፡-

72.በኢኒስቲትዩቱ በእንስሳት ጀርባ ላይ የሚቀባ ኬሚካል መጠን አጠቃቀም ስርዓት ሊዘረጋና ተፈጻሚነቱ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡

73.በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፣

- ✓ በእንስሳት ጀርባ ላይ የሚቀባን ኬሚካል መጠን በተመለከተ በፕሮጀክቱ የተዘረጋ ስርዓት ባይኖርም በኬሚካል አምራቹ ድርጅት በኬሚካሉ ዕቃ ላይ በፅሁፍ የተቀመጡ መስፈርቶች እንዳሉ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ነገር ግን በናሙና ባየናቸው 3ት ቀበሌዎች የእንስሳት የኬሚካል ርጭት ላይ ክብደታቸው ትልቅ ለሆኑ ከብቶች እስከ 20ሚሊ ሊትር፣ ክብደታቸው ትንሽ ለሆኑ ከብቶች 10 ሚሊ ሊትር እንዲቀባ እንዲሁም የቆላ ዝንቦች በጥቁር ቀለም ስለሚሳቡ ቀለማቸው ጥቁር ለሆኑ ከብቶች በዛ ያለ ኬሚካል እንዲቀቡ መስፈርት ያስቀመጠ ቢሆንም፤ ክብደታቸው አነስተኛ ለሆኑ እና ክብደታቸውትልቅ ለሆኑ ከብቶችተመሳሳይ የኬሚካል መጠን መጠቀማቸው፣ ቀለማቸው ጥቁር ለሆኑ ከብቶች እና ከጥቁር ውጭ ሌላ ቀለም ላላቸው

ከብቶች ተመሳሳይ መጠን መቀባታቸው በተጨማሪም ከብቶችን ስርዓት ባለው መልኩ ለመቀባት የሚያስችል በረት አለመዘጋጀቱና ያሉት በረቶች በአካባቢው ካሉት ከብቶች ቁጥር ጋር ተመጣጣኝ ባለመሆኑ ከብቶችን በአብዛኛው ከበረት ውጪ በማሯሯጥ የሚቀቡ መሆኑ በኦዲቱ የመስክ ጉብኝት ወቅት ለማየት ተችሏል፡፡

- ✓ ይህን በማስመልከት የመስክ ኦፕሬሽን ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ተጠይቀው በሰጡት መልስ፤ ኬሚካሉ የሚረጨው ከብቶቹ ባላቸው ክብደት መጠን መሆኑን፣ በአብዛኛው ለትልልቅ ከብቶች 20 ሚሊ እና 30 ሚሊ ሆኖ እንደሚሰጥ እና ምናልባት አንዳንድ አርሶአደሮች ይህንን ስህተት ካልፈጠሩ በስተቀር በአብዛኛው ትንንሽ ጥጆች እንዲያውም መቀባት እንደሌለባቸውና ምክንያቱም የቆላዝንብ አብዛኛውን ጊዜ ትልልቅ ከብቶችን ስለምትመርጥና ጥጆችም ርቀው ወደ ጫካ ስለማይጓዙ እንደሆነና በከብቶች ላይ የሚረጨው ኬሚካል አንዴ የተረጨው ቢያንስ ለ1 ወር የመከላከል አቅም እንዳለው እና ይህ ርጭት በተከታታይ ያልተደረገው በግዢ መጓተት ምክንያት ረጅም ጊዜ ስለወሰደ በዚህ መሐከል ክፍተት/መቋረጥ/ ሊኖር እንደቻለና ከህዳር 2004 ዓ.ም ጀምሮ ኬሚካል እየቀረበ በመሆኑ መቆራረጥ እንደማይኖር ገልፀዋል፡፡
- ✓ የፕጀሮክት ጽ/ቤቱ ዋና ዳይሬክተር ስለጉዳዩ በሰጡት ምላሽ፤ ፕሮጀክቱ በአመት ከአንድ እስከ ሁለት ሚሊዮን የሚደርሱ እንስሳት በኬሚካል እንደሚቀቡ፣ በዚህም ምክንያት ሁሉንም ከብቶች ሚዛን ላይ እያወጡ በኪሎ ለመለየት አዳጋች በመሆኑ እና ሙያው ጠለቅ ያለ አሰራርን የሚጠይቅና ሥራው በሕብረተሰቡም ተሳትፎ ጭምር የሚከናወን በመሆኑ መጠነኛ ግድፈቶች ሊኖሩ ቢችሉም፤ ኬሚካሉ አላግባብ ጥቅም ላይ ውሏል ለማለት እንደማያስችል ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም አምራች ድርጅቱ ባስቀመጠው መስፈርት መሰረት በተከታታይ ለምን እንደማይቀባ ሲገልፁ፤ በከብቶች ላይ የሚቀባው ኬሚካል የጊዜውን ገደብ /Application data intervals/ በተለያዩ 32 ነጥቦች ላይ ጥገኛ ሊሆን/depend on many factors/ እንደሚችልና ከነዚህም መሐከል በአካባቢው ያለው የእንስሳት ቁጥር ብዛት፣ በአካባቢው የቆላ ዝንብ መጠንና አይነት፣የአካባቢው

ተፈጥሮአዊ አቀማመጥ፣ የአየር ጸባይ/ዝናብ ወይስ ፀሐይ/፣ ያለው የመድሐኒት አቅርቦትና መጠን በመሳሰሉት ጥገኛ ቢሆንም መድሃኒቱ ባላቸው ጊዜ ወቅቱን ጠብቀው እርጭት እንደሚያደርጉ አስታውቀዋል፡፡

- ✓ ይሁንና በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩ ቦታዎች ለትንንሽ ጥጆች እና ለትልልቅ ከብቶች የሚቀባው የኬሚካል መጠን አንድ አይነት መሆኑና ስራውእየተሠራለት ላለው ለህብረተሰብ አካል አስፈላጊው ስልጠና ባለመሰጠቱ እና ህብረተሰቡ በቂ በረቶች እንዲሰራ ባለመደረጉ ከብቶችን እያሯሯጠ በሚቀባበት ወቅት ኬሚካል ከከብቱ ጀርባ ውጭ የሚባክን መሆኑ ታይቷል፡፡
- ✓ በዚህም ምክንያት በከብቶች ጀርባ ላይ የሚቀባው የኬሚካል አጠቃቀም ብቃት ባለው መልኩ እየተከናወነ አለመሆኑን እና የቅቢው ሂደትም የኬሚካል ብክነትን እያስከተለ መሆኑን የኬሚካል ቅቢ ሲደረግባቸው በነበሩ በወላይታ ሶዶ አባላ ፋራቶ ቀበሌ፤ በአርባ ምንጭ ዘይሴ ወዘቃ ቀበሌ እና በዲላ ዱቢቻ ቀበሌ በማየት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡
- ✓ እንደዚሁም የቆላ ዝንብ ባለባቸው አካባቢዎች የሚደረገው የኬሚካል እርጭት ወቅቱን የጠበቀ አለመሆኑን እና የጊዜ ገደብ ተቀምጦለት የሚከናወን ባለመሆኑ ያካባቢው ህብረተሰብ ኬሚካሉ በሚረጭበት ወቅት ከብቶቹ በበሽታ እንደማይጠቁ እና ኬሚካሉ በዘገየ ጊዜ ዝንቦች ተመልሰው ስለሚራቡ ከብቶች በዝንቦች ተነድፈው ለገንዲ በሽታ እንዲጋለጡ እያደረገ ይገኛል፡፡

74.በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተሰጠው የማሻሻያ ሃሳብ ተግባራዊ የተደረገ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

- ➢ በዲላ ከብቶቹ ላይ የሚቀባው ኬሚካል በግምት እንደሆነ ፣20 ሚሊ ሊትር 200 ኪሎ ግራም ለሆኑ ከብቶች እንደሚቀቡ፣ 10 ሚሊ ሊትር 100 ኪሎ ግራም ለሆኑ ሲሆን የሚሰሩትም የኬሚካሉ እቃው ላይ ባለው የአጠቃቀም መመሪያ መሰረት መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡
- ➢ በአርባምንጭ ዙሪያ ቆላ ሻራ ቀበሌ እና ጫኖ ዶርጋ ቀበሌ በመስክ ምልከታ ወቅት ለመመልከት እንደተቻለው በከብቶች ጀርባ ላይ ኬሚካል

የሚቀባው በግምት መሆኑን፣ ለትልልቅ ከብቶችም ለትንሽም ጥጆችም ተመሳሳይ የሆነ የኬሚካል መጠን እንደሚቀቡ፣ በከብቶች ጀርባ ላይ ኬሚካል በሚቀባበት ወቅት ባለሞያው በሬዎችን በመሳት ወደ መሬት በመርጨት የኬሚካል ብክንት መኖሩ ታውቋል፡፡ ስለ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በእንስሳት ጀርባ ላይ የሚቀባ ኬሚካል መጠን አጠቃቀምን በተመለከተ በኢኒስቲትዩቱ የተዘረጋ ስርዓት የሌለ መሆኑን፣ ስለ ኬሚካሉ አጠቃቀማቸው በኬሚካል እቃው ላይ ባለው መሰረት እንደሆነ፣ ለትላልቅ ከብቶች 20 ሚሊ ሊትር፣ለትናንሽ ከብቶች ደግሞ 10 እና 15 ሚሊ ሊትር እንደሆነ፣ የከብቶችን ክብደት የሚለዩት በግምት እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል፡፡

75.በጫኖ ዶርጋ ቀበሌ በከብቶች ጀርባ ላይ ኬሚካል በሚቀባበት ወቅት ኬሚካል በመቀባት ላይ ያለው ባለሞያ ምንም ዓይነት መከላከያ ጓንት ሳይጠቀም በእጁ እየቀባ መሆኑን ለመመልከት ተችሏል፡፡በተጨማሪም ከበረት ውጪ ከከብቶች ጋር እየተሯሯጠ በሚቀባበት ወቅት በሬዎችን በመሳት ወደ መሬት በመርጨት ከፍተኛ የሆነ የኬሚካል ብክንት እንዳለ የኦዲት ቡድኑ ለመመልከት ችሏል፡፡



*ሥዕል5፡- በአርባምንጭጫኖ ዶርጋ ቀበሌ በከብቶች ጀርባ ኬሚካል ሲቀባ ብክነት*

76. በመሆኑን በእንስሳት ጀርባ ላይ የሚቀባ ኬሚካል መጠን አጠቃቀም ስርዓት ባለመዘርጋቱ በከፍተኛ ወጪ በውጭ ምንዛሪ የተገዙ ኬሚካሎች እንዲባክኑ አድርጓል፡፡

**በቆላ ዝንብን ለማጥፋት ለሚሳተፉ የማህበረሰብ አካላት የሚሰጥ ስልጠናን እና ለእንስሳት መቀቢያ የሚያገለግሉ በአካባቢው ከሚገኙ ቁሳቁሶች የተሰሩ በረቶችን በተመለከተ :-**

77.በቆላ ዝንብን ለማጥፋት በመስክ ስራ ላይ ለሚሳተፉ የማህበረሰብ አካላት ወደ ሥራ ከመሰማራታቸው በፊት ተገቢው ሥልጠና ሊሰጣቸው ይገባል፡፡በመስክ ሥራ ለእንስሳት መቀቢያ የሚያገለግሉ በአካባቢው ከሚገኙ ቁሳቁሶች የተሰሩ በረቶች ሊዘጋጁና ስራ ላይ ሊውሉ ይገባል፡፡

78.በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

- ✓ በኦዲቱ ወቅት በተመለከትናቸው ወላይታ ሶዶ፣ አርባምንጭና ዲላ ጣቢያዎች ከማህበረሰብ ለተውጣጡ አካላት የሚሰጡ ስልጠናዎች እንዳሉ ቢገለፅም፤ መረጃ ተጠይቀው ሊቀርቡ አልቻሉም፡፡ በተጨማሪም ስልጠናዎች በተወሰኑ ጊዜያት 33 የማይሰጡ በመሆናቸው ማህበረሰቡ አንዴ የሰለጠነውን በመዘንጋት ብዙ ችግሮች ሊፈጠሩ ይችላሉ፡፡
- ✓ በታርጌት ተከላና በእንስሳት ጀርባ ላይ የኬሚካል ርጭትን በተመለከተ ለማህበረሰቡ የተሰጡ ስልጠናዎች ለመኖራቸው የተገለፀ ቢሆኑም፤ የሚሰጡት ስልጠናዎች ተከታታይነት የሌላቸውና የግንዛቤ ማስጨበጫ ለህብረተሰቡ በተለያዩ ሚዲያዎችና መንገዶች ባለመሰጠታቸው ምክንያት የዝንቡ መጠን ትንሽ ሲቀንስ ዝንቡ የጠፋ ስለሚመስላቸው ወይም መዘናጋት በመፈጠሩ ታርጌቶችን ነቅለው መውሰድ፣ ታርጌቶችን በደንብ አለመትከል የመሳሰሉት ችግሮች ይፈጠራሉ፡፡
- ✓ በሌላም በኩል በእርባታ ማዕከሉ ለሚገኙ ባለሞያዎች የሚሰጡ ስልጠናዎች እንዳሉ ከተከለሱ መረጃዎች ቢታወቅም የሚሰጡት በቂ ባለመሆናቸው የሰራተኛ ክህሎት ችግር እንዳለ እና ስልጠና እንደሚያስፈልግ ከ2004 ዓ.ም የ6 ወር የአፈፃፀም ሪፖርት ላይ ታውቋል፡፡ ምንም እንኳን የውጭ ሥልጠናን በተመለከተ ከተከሰቱት ችግሮች አኳያ በመንግስት አቅጣጫ የተሰጠ መሆኑ በቃል ቢገለጽም፤የዝንቦች እርባታ በጣም ጥንቃቄ የሚያስፈልገው እና በትኩረት ሊሰራ የሚገባው በመሆኑ የውጭ ሥልጠና በሀገር ውስጥ ስልጠናዎች/ግንዛቤ ማስጨበጫ/ ተተክቶ ለባለሞያዎች

በተከታታይ ካልተሰጠ እርባታው ላይ ከፍተኛ ችግር /በዝንቦች/ ላይ የሞት አደጋ ቁጥር እንዲጨምር ያደርገዋል፡፡

- ✓ ሌላው በመስክ በተመለከትንባቸው አካባቢዎች የኬሚካል ርጭት ሲካሄድ ሁሉም ከብቶች በተመሳሳይ መጠን መቀባታቸው ለሚቀቡት የማህበረሰብ አካላት ተከታታይነት ያለው ስልጠና አለመሰጠቱን ያሳያል፡
- ✓ ይህንን በተመለከተ የፕሮጀክት ማስተባበሪያ ቢሮ ኃላፊውን ተጠይቀው በሰጡት መልስ፤ ኬሚካሉ የሚቀባው ከብቶቹ ባላቸው ክብደት መጠንና ትንንሽ ጥጆች የማይቀቡ ሲሆን ነገር ግን የርጭት ተግባሩን የሚያከናውኑ አርሶአደሮች የኬሚካል ርጭት ተግባሩ ላይ ስህተት ፈጥረው ካልሆነ በስተቀር ሁሉም አንድ አይነት እንደማይቀቡ ገልፀዋል፡፡
- ✓ ከብቶችን ስርዓት ባለው መልኩ ለመቀባት የሚያስችል በረት አለመዘጋጀቱና ያሉት በረቶች በአካባቢው ካሉት ከብቶች ቁጥር ጋር ተመጣጣኝ ባለመሆኑ ከብቶችን በአብዛኛው ከበረት ውጪ በማሯሯጥ የሚቀቡ መሆኑ በኦዲቱ የመስክ ጉብኝት ወቅት ለማየት ተችሏል፡፡

79.በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተሰጠው የማሻሻያ ሃሳብ ተግባራዊ የተደረገ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

- ➢ ኢኒስቲዩቱ የሚሰራው ስራ በጣም ሰፊና በቂ ግንዛቤ በየደረጃው የሚጠይቅ እንደመሆኑ መጠን ለህብረተሰቡ በቂ ስልጠና አለመሰጠቱን ፤ በፕሮጀክቱ በተሰጠው ስልጠና የዞንና የወረዳ አመራሮቹ ከተሳተፉ በኋላ የወሰዱትን ስልጠና ቀበሌ ወርደው የማያሰለጥኑ መሆኑንና ከአንዱ አከባቢ የተገኙ ተሞክሮዎችን ቀምሮ ወደ ሌላ ማስተላለፍ አለመቻል፤ እንዲሁም አከባቢው የአርብቶ አደር አከባቢ እንደመሆኑ መጠን አመራሩ በሌሎች አከባቢዎች የሚሰራውን የማስፋት ተግባር በዚሁ አከባቢ ከሀገሪቱ የእንስሳት ሀብት አኳያ በተቃኘ መልኩ መስራት አለመቻሉን ለማወቅ ተችሏል፡፡
- ➢ በአንዳንድ ክፍሎች በአዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ላይ ስልጠና በአገር ውስጥ ባለመኖሩ በቂ ስልጠና ያለማግኘታቸው፣ በደቡብ መስክ ኦፕሬሽን ከአለም አቀፍ የምግብና የእርሻ ልማት ድርጅት /FAO/ ጋር በመተባበር በአርባምጭ

ከተማ ስለ ቆላ ዝንብና ሌሎች ተናካሽ ነፍሳትን ለመከላከል የሚያስችል በኬሚካል የተነከሩ መረቦችን በመጠቀም የእንስሳት ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ በሚያስችልበት ሁኔታ ላይ ያተኮረ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ከጋሞጎፋ ዞን ከአርባምንጭ ዙሪያና ከምዕራብ አባያ ወረዳ ለተውጣጡ አርሶ አደሮችና የግብርና ባለሞያዎች እንዲሁም በኢኒስቲትዩቱ አዲስ ለታቀፈው በባስኬቶ ልዩ ወረዳ ስለ ቆላ ዝንብና የገንዲ በሽታ ቁጥጥር ላይ አስመልክቶ ለ 120 መካከለኛ አመራር አካላት ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ 21 አመራር አካላት ስልጠና በመስጠት የእቅዱ አፈፃፀም 17.5 % መሆኑ፤ ለ 300 የልማት ሰራተኞች ለቀበሌ አመራር አካላት ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ 138 ስልጠና የተሰጠ ሲሆን የእቅዱ አፈፃፀም 46 % መሆኑን ከኢኒስቲትዩቱ የ2008 በጀት ዓመት የውጤት ተኮር እቅድ ታውቋል፡፡

80. በዲላ በቆላ ዝንብ የማጥፋት ስራ ላይ ለሚሳተፉ የማህበረሰብ አካላት ስልጠናዎችን እንደሚሰጡ ነገር ግንበ 2007 ዓ.ም እና በ2008 ዓ.ም ስልጠናዎች ያልተሰጣቸው መሆኑን፣ ለባለሞያዎችም በ 2007 ዓ.ም እና በ 2008 ዓ.ም ስልጠና ያልተሰጣቸው መሆኑን ታውቋል፡፡

81. በአርባምንጭ ማዕከል በቆላ ዝንብ የማጥፋት ስራ ላይ ለሚሳተፉ የማህበረሰብ አካላት ወደ ስራ ከመግባታቸው በፊት ስልጠና እንደሚሰጣቸው ፣ ስልጠና የሚሰጠውም በዓመት አንድ ወይም ሁለት ጊዜ መሆኑን፣ ለባለሞያዎች በ 2007 ዓ.ም ስልጠና ያልተሰጠ መሆኑን በ 2008 ዓ.ም ጂ አይ ኤስ ላይ ለአንድ ባለሞያ ብቻ ስልጠና የተሰጠ መሆኑን፣ የስልጥና ክፍተት መኖሩን እንዲሁም ስልጠና ላይ ግልፀኝነት የሚጎድል መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

82. በቆላ ዝንብን ለማጥፋት በመስክ ስራ ላይ ለሚሳተፉ የማህበረሰብ አካላት ወደ ሥራ ከመሰማራታቸው በፊት ተገቢው ሥልጠና አለመሰጠቱ ስራው በተገቢው መንገድ በጥራት እንዳይሰራ አድርጓል፡፡

83. አርባምንጭ ዙሪያ ቆላ ሻራ ቀበሌ የሚገኘው በረት ከእንጨት የተሰራ ሲሆን ባልተስተካከል መልኩ ስለተሰራ ከብቶች እየሾለኩ እንደሚወጡበት፣ የበረቱ መሬት ጭቃ በመሆኑ ከብቶች ኬሚካል በሚቀቡበት ወቅት በአግባቡ ለመራመድ ሲቸገሩ ለማየት ተችሏል፡፡ በተለይም ትናንሽ ከብቶች መራመድ ሲያቅታቸው የኦዲት ቡድኑ ተመልክቷል፡፡እንዲሁም በአርባምንጭ ዙሪያ ጫኖ ዶርጋ ቀበሌ የሚገኘው

በረት ከእንጨት የተሰራ ሲሆን ባልተስተካከለ መልኩ ስለተሰራ ከብቶችን የሚያሾልክ መሆኑን ለመመልከት ተችሏል፡፡



*ሥዕል 6፡- በአርባምንጭ ቆላ ሻራ ቀበሌ ለከብቶች ኬሚካል መቀቢያ በረት ለስራ አመቺ አለመሆን*

84.በመሆኑም በመስክ ሥራ ለእንስሳት መቀቢያ የሚያገለግሉ በአካባቢው ከሚገኙ ቁሳቁሶች የተሰሩ በረቶች ለስራ አመቺ ባለመሆናቸው የኬሚካል ብክንት እንዲፈጠር አድርጓል፡፡

## በኢኒስቲትዩቱ የተጠናከረ የመረጃ አያያዝ ስለመኖሩእና በቆላ ዝንቦች እርባታ ወቅት ለሚከሰቱ የሞት አደጋዎች መንስኤ እና የመፍትሄ ሃሳቦች በመረጃ ስለመያዙ ፡-

85.በኢኒስቲትዩቱ ለሚደረጉ የክትትልና ግምገማ ሥራ እንዲሁም ለሚደረጉ የምርምር ጥናቶች በመነሻነት የሚያገለግል የመረጃ አያያዝ ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡በኢኒስቲትዩቱ በቆላ ዝንቦች እርባታ ወቅት ለሚከሰቱ የሞት አደጋዎች መንስኤ የሆኑ ጉዳዮች እና የመፍትሄ ሃሳቦች ተዘጋጅተው በመረጃ ሊያዙ እንዲሁም ተግባራዊ ሊደረጉ ይገባል፡፡

86.በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፣

- ✓ በኦዲቱ ወቅት፣ በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በዝንብ እርባታ ክፍል ውስጥ በተለያዩ ጊዜያት የዝንቦች የሞት አደጋ ያጋጠመ መሆኑ ቢታወቅም፣ ለመሞታቸው መንስኤ የሆኑ ጉዳዮች እና የመፍትሄ ሃሳቦች ተዘጋጅተው በመረጃ አለመያዛቸው በተጨማሪም በ2001 ለሙከራ የተለቀቁ ብዛታቸው 8,000 የሚሆኑ የመከኑ ወንድ የቆላ ዝንቦች ስላስገኙት ውጤት በመረጃ ተጠናቅሮ አለመያዙ፣ የኘሮጀክት ማዕከሉ በተያዘለት10 ዓመት ጊዜ ውስጥ ዓላማውን(ግቡን) ያልመታበትን(ያላሳካበትን) ምክንያት የሚያሳይ መረጃ/ሪፖርት/፣ በየሩብ ዓመቱ የሚዘጋጁ የሥራ አፈፃፀምሪፖርቶች፣ በማዕከሉ ሀሙስ ሀሙስ የማራቢያ ክፍሉን በተመለከተ የሚደረግ የግምገማ ስብሰባ (ቃለጉባኤ) እና ሰኔ 2003 ዓ.ም. ስለኘሮጀክቱ ዓለም አቀፋዊ ወርክሾኘ የተደረገውን ስብሰባ የመሳሰሉት መረጃዎች እንዲቀርቡ ተጠይቀው ሊቀርቡ አልቻሉም፡፡
- ✓ በተጨማሪም በ3ቱም/በወላይታ ሶዶ፣ በአርባምንጭ እና በዲላ/ ጣቢያዎችም እያንዳንዳቸው በስራቸው የሚይዟቸው ወረዳዎች ውስጥ ያሉትን የከብት ብዛት የሚገልጽ መረጃና ለልማት ጣቢያዎችና ለወረዳዎች ስልጠና እንደተሰጠ በሪፖርቶች ቢገለጽም የተሰጠው ስልጠና ዓይነት፣የሰለጠኑት ሰዎች ብዛት የመሳሰሉትን የሚገልጽ መረጃ ተጠይቆ ሊቀርብልን አልቻለም፡ ፡

- ✓ የክልል ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ኃላፊ ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት መልስ፤ ወደ መስክ በ2001 ዓ.ም የተረጩ ዝንቦችን መረጃ በተመለከተ ዝንቦቹ ተለቀው ጫካ ውስጥ ካሉ ዝንቦች ተወዳድረው ውጤታማ መሆናቸውን የሚገልጽ መረጃ ከብሔራዊ ጽ/ቤቱ ማግኘት እንደሚቻል ገልፀዋል፡፡ የከብቶች ብዛት ለምን ተመዝግቦ እንዳልተያዘም የከብቶች ቁጥር መረጃ የሚገኘው በግብርና ጽ/ቤት በኩል መሆኑንና መረጃን በየጊዜው እንዲይዙ ቢጠየቁም፤ አንዳንድ የተፋለሰ መረጃዎች እንደሚቀርቡና ለወደፊቱ እንደሚስተካከል ጥረት እንደሚያደርጉ አስረድተዋል፡፡
- ✓ ስለሁኔታው የፕሮጀክቱን ጽ/ቤት ኃላፊ ዋና ዳይሬክተር እንደ ገለፁት፤ በፕሮጀክት ማዕከሉ፣ በማስተባበሪያውና በጣቢያዎች መረጃዎች በአግባቡ እንደተያዙ ገልፀዋል፡፡ 35111. የፕሮጀክት ጽ/ቤት ሃላፊ ይህን ይበሉ እንጂ ዝንቦች ከተቀመጠው ሳይንሳዊ የሞት መጠን ከፍ ባለ ሁኔታ በሚሞቱበት ወቅት የሞቱበት ምክንያት ተጠንቶ በመረጃ ያልተያዘ መሆኑ፣ መስክ ላይ የተለቀቁ ዝንቦች መረጃ ከፕሮጀክት ጽ/ቤቱ እንደምናገኝ ቢገለፅልንም ያልቀረበ መሆኑ፣ ባጠቃላይ ከላይ የተጠቀሱት ሁሉ መረጃ እንዲቀርቡ ቢጠየቁም አለመቅረባቸው የፕሮጀክቱ የመረጃ አያያዝ የተጠናከረ አለመሆኑን የሚያሳይ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በተጨማሪም የክትትልና የመረጃ አያያዝ በተመለከተ በሁሉም የስራ ክፍሎች ድክመት እንዳለ ከ2004 ዓ.ም የ6 ወር አፈፃፀም ግምገማ ሪፖርት ላይ በተጨማሪ ለማወቅ ተችሏል፡፡
- ✓ ይሁን እንጂ በእኛ አስተያየት በፕሮጀክት ማዕከሉ የተጠናከረ መረጃ ሥርዓት አለመኖሩ ችግሮች በግልጽ እንዳይታዩና ወቅታዊ መፍትሄ እንዳያገኙና ፕሮጀክቱ በሚሰራባቸው አካባቢዎች ያሉ ከብቶች ብዛት በመረጃ አለመያዙ ለየወረዳው የሚያስፈልገውን የኬሚካልመጠን እንዳይታወቅ ሊያደርግ እንደሚችል ይታመናል፡፡

87.በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተሰጠው የማሻሻያ ሃሳብ ተግባራዊ የተደረገ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

- በኢኒስቲትዩቱ የመረጃ አያያዝ ወቅታዊ የስብሰባ ፕሮግራምና የስብሰባ ቃለጉባኤ አያያዝ ፣ የምዘና አሰጣጥ ስርዓት፣ የግብረመልስ አሰጣጥ ፣ ወቅቱን የጠበቀ ሪፖርት አላላክ በኩል ጅምሮች ተጠናክረው የቀጠሉ ቢሆንም አሁንም ሙሉ በሙሉ የተቀረፈ ችግር አለመሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡
- መክነው የተለቀቁ የቆላ ዝንቦች ያስገኙት ለውጥና ውጤትን በተመለከተ ተከታታይ ጥናት አለመደረጉና ግብረ መልስ አለመኖሩ፣የሳይንስ መገናኛና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሪፖርት ለማወቅ ተችሏል፤፤
- በኢኒስቲትዩቱ የመረጃ አያያዝ፣ ወቅታዊ የስብሰባ ፕሮግራምና የስብሰበ ቃለ ጉባዔ አያያዝ፣ የምዘና አሰጣጥ ስርዓት፣ የግብረመልስ አሰጣጥ፣ ወቅቱን የጠበቀ ሪፖርት አላላክ በኩል ጅምሮች ተጠናክረው የቀጠሉ ቢሆንም አሁንም ትኩረት የሚሻ መሆኑ፣ ዳታ ቤዝ በማስገባትና በማደራጀት የስርዓተ ሰነድ አገልግሎትን ፈጣን በሆነና በአይ ሲቲ በታገዘ ድጋፍ የማጠናከር ሥራ አለመከናወኑ፣ እናመረጃዎችን በኦን ላየን የማሰራጨትና የመቀበል ስርዓት የመዘርጋት ሥራ አለመከናወኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡
- በቆላ ዝንብ ማርባት እና ማምከን ላይ 55 % የተሰራ መሆኑን በአጠቃላይ እቅዱ በብሄራዊ ፅ/ቤት 50 % መሆኑን፣ የክትትልና የመረጃ አያያዝ ችግሮች መኖራቸውን፣የተላኩት የዝንብ ቁጥሮች አሳሳች መሆኑን፣ እቅዶቹን በሚፈለገው በጥራት አለመፈፀማቸውን፣ የግብረ መልስ አሰጣጥና የመረጃ አያያዝ ክፍተቶች መኖራቸውን ፣ ለዝንቦች ምገባ የሚቀርብ ደምን በተመለከተ ደረጃውን ያልጠበቀና እንዲያውም ሽታ ያለው ደም መቅረቡ ከቡድኖች መቅረቡን፣ሽታ ያለው አንድ ፕላስቲክ ደም መገኘቱን፤ የሞጁል ሁለት ቡድኖች ደም ከላብራቶሪ አንድ ለመውሰድ ስለሚያጠራጥራቸው ደም የሚወስዱት ከሞጁል አንድ መሆኑን፤ይህም ደግሞ የደም እጥረት እያስከተለ መሆኑን፤የደሙን የጥራት ደረጃ በተመለከተ ለማጣራት በማለት ሽታ የፈጠረበትን ባች ቼክ ለማድረግ በኳሊቲ ኮንትሮል ሁለት ባክቴሪያል ኮለኒ የተገኘ መሆኑን ፣ ዝንቡ እያለ ፑፔው ግን እየሰጠ አለመሆኑን ፣የዝንቡ ቁጥር ባለበት ሆኖ ባልታወቀ ሁኔታ ፑፔ እየቀነሰባቸው መሆኑን፣ በአጠቃላይ ባለው ሁኔታ የቆላ ዝንብ ቁጥር በየትኛውም ቡድን ቢሆንም የወረደ መሆኑን፣በተጨማሪም ያንግ ዝንቦች ላይ በተለይም ወንዶች ላይ

የመሞት ሁኔታ መከሰቱ በ2005 ዓ.ም ከተደረገ ከማኔጅመን ስብሰባ ቃለ-ጉባኤ ታውቋል፡፡

88.የቃሊቱ የእርባታ ክፍል ሀላፊ ስለጉዳዩ ተጠይቀው ወደ ስራው ከመጡ አንድ ዓመታቸው እንደሆነ እና ስራ ከጀምሩ ጀምሮ ምንም የዝንብ ሞት እንዳልተከሰተ፣ ነገር ግን ኢኒስቲትዩቱ ከፕሮጀክት ወደ ኢኒስቲትዩት በሚሸጋገርበት ወቅት ቀድሞ የነበሩ ሰራተኞች ስራውን ለቀው ሌላ ሰራተኛ በሚቀጠርበት የሽግግር ጊዜ ብዙ ዝንቦች የሞቱ መሆኑን፣ ስራቸውን እንደ አዲስ ከ ዜሮ የጀመሩ መሆኑን ፣ስራውን ሲጀምሩ የነበረው የዝንብ ቁጥር ዜሮ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

89.በኢንስቲትዩቱየመረጃ አያያዝ ክፍተቶች በመኖራቸው ግልጽ፣ ወጥ የሆነና የማይጣረዝ መረጃ እንዳይገኝ አድርጓል፡፡

## ከባለድርሻ አካላት ጋር ስለሚደረግ የመረጃ ልውውጥ ፡-

90.ኢኒስቲትዩቱ ከባለድርሻ አካላት ጋር የልምድ ልውውጥ የሚያደርግበት፣በቆላ ዝንቦች እርባታ ወቅት ለሚከሰቱ ችግሮች ወቅታዊ የሆኑ የምርምር ስራዎችን የሚሰራበት መደበኛ የሆነና የተቀናጀ የመረጃ ልውውጥ ስርዓት ሊኖረው ይገባል፡፡

91.በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

- ✓ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ስራውን በደቡብ ክልል ሲጀምር ከክልሉ የግብርና ቢሮ ጋር በቅንጅት መስራት የሚያስችለውን የስምምነት ሰነድ በክልሉ ርዕሰ መስተዳደር፤ በክልሉ የግብርና ቢሮ ኃላፊ እና በፕሮጀክቱ ጽ/ቤቱ ኃላፊ ተፈርሞ በወቅቱ ከነበረውሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ኮሚሽነር ይሁንታ ያገኘ ሰነድ ቢኖርም ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በይበልጥ በቅንጅት መስራት ካለበት ከክልሉ ግብርና ቢሮ እና ከግብርና ሚኒስቴር ጋር መረጃዎችን የማይለዋወጥ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡
- ✓ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በዋነኝነት ከሚያከናውናቸው ስራዎች ውስጥ በሚንቀሳቀስባቸው ወረዳዎች እና ቀበሌዎች በገንዲ በሽታ የተጠቁ እንስሳትን ህክምና መስጠት ሲሆን ይህን በመረጃ በማጠናከር ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በዋነኝነትም ከክልሉ የግብርና ቢሮ ጋር መረጃውን መለዋወጥ ይኖርበታል፡፡ ይሁንእንጂ ይህ ስራ ከክልሉግብርና ቢሮጋር በቅንጅት ባለመሰራቱ በ2003 ዓ.ም ዓመታዊ

ሪፖርት መሰረት 36የክልሉየግብርና ቢሮ ፕሮጀክቱ በሚንቀሳቀስበት አካባቢ ብቻ 450,000 በገንዲየተጠቁ ከብቶች ማከሙ የተጠቀሰ ሲሆን በሌላ በኩል፤ የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በ2003 ዓ.ም. የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርቱ ላይ ግን ለ97,625 እንስሳት የገንዲ በሽታ መድሐኒትሕክምና መስጠቱ ገልፀዋል፡፡ ይህ የመረጃ ልውውጥ ክፍተት መኖሩን ከማሳየቱም በላይ በቅንጅት ቢሰራ ያስገኝ የነበረውን ጥቅም እንዳያገኝ ምክንያት መሆኑን ያመለክታል፡፡በተጨማሪም የክልሉ የግብርና ቢሮ በራሱ የቆላ ዝንቦችን ለመግደል የሚያገለግል ታርጌት ተከላ የሚሰራ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

- ✓ የመረጃ ልውውጥን በተመለከተ በአዋሳ የክልሉ የእንስሳት ሀኪም የሰጡት ምላሽየመረጃና የሪፖርት ልውውጥ ከክልል ኘሮጀክቱ ጋር እንደሚያደርጉ በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ የገለፁ ቢሆንም መረጃ ተጠይቀው አላቀረቡም፡፡
- ✓ የማስተባበሪያ ጽ/ቤት ኃላፊ ኘሮጀክቱ በሚሰራባቸው ወረዳዎች የቆላ ዝንብና የገንዲበሽታ መቀነሱንና በክልሉ ግብርና ቢሮ ለገንዲ በሽታ ህክምና ተሰጠ ተብሎ የተቀመጠው አሃዝ/450,000/ የክልሉን ሙሉ ሽፋን የሚያሳይ ሊሆን እንደሚችልና በግብርና የሚሰጠው ህክምና የላብራቶሪ ምርመራ ድጋፍን መሠረት ያላደረገ በመሆኑ ስህተትም ሊፈጠር እንደሚችል ገልፀዋል፡፡ ማስተባበሪያ ጽ/ቤቱ ያከናወነውን ሥራዎች ማለትም በገንዲ በሽታና የቆላ ዝንብ ቅነሳን በተመለከተ ለግብርና ሪፖርት እንደሚያደርጉና በአንፃሩ ግብርናዎች በአብዛኛው የተለያዩ ሥራዎች ስለሚሰሩና በገንዲ ህክምና ላይ ስለማያተኩሩ አልፎ አልፎ በአንዳንድ ወረዳዎች የታርጌት ተከላና ቅብ በተመለከተ የመረጃ ልውውጥ እንደሚደረግና የጐደለውንም ነገር እገዛና ድጋፍ እንደሚያደርጉ ገልፀዋል፡፡
- ✓ የፕሮጀክቱ ዋና ዳይሬክተር ስለዚሁ ጉዳይ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፤ በወሳኝነት በቆላ ዝንብ እና በገንዲ በሽታ ላይ ፕሮጀክቱ በሚንቀሳቀስባቸው አካባቢዎች የሚሰራው ይህ ፕሮጀክት መሆኑን እና የሚሰራውም ብቻውን ሳይሆን ከግብርና ባለሙያዎችና ከህብረተሰቡ ጋር በመሆኑ የተሰራውን የስራ ሪፖርቶች ያገኛሉ፡፡ ለክልሉም በየሩብ አመቱ ሪፖርት እንደሚያቀርቡና ከግብርና ቢሮ ግን ለፕሮጀክቱ ለገንዲ በሽታ የተሰጡ የህክምና ሪፖርቶች እንደማይቀርቡ ሆኖም ግን በፕሮጀክቱ አካባቢ

በጋራ የተሰሩ የቆላዝንብ ቁጥጥር ስራዎች ታርጌት በኬሚካል መቀባት እና ተከላ፣ በከብቶች ላይ የኬሚካልቅቢ ግብዓቶች ከግብርና ቢቀርቡም እንኳን በተሰሩ ስራዎች ላይ የመረጃ ልውውጥይደረጋል፡፡ ይህ የሚሆነው እነኚህ ሥራዎች ከተሰሩ እንጂ ይህንን ሥራ የሚሰራው 37 ፕሮጀክቱ በመሆኑና በተጨማሪም 450,000 የሚያህል እንስሳት ፕሮጀክቱ በሚንቀሳቀስበት አካባቢ የገንዲ ህክምና ተሰጥቷል የሚል ግምት የሌላቸውና በግብርናጽ/ቤት የሚሰጠው የገንዲ ህክምና በአብዛኛው በላብራቶሪ ምርመራ የተደገፈ ባለመሆኑና ገንዲ ባለባቸው አካባቢዎች በግምት ህክምናው ስለሚሰጥ የታከመው ሁሉ በገንዲ በሽታ ተጠቅቶ ነው ለማለት አያስደፍርም የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

- ✓ ይሁንና በኦዲቱ ወቅት እንደተገነዘብነው ከባለድርሻ አካላት ጋር የተቀናጀ የመረጃ ልውውጥ አለመኖሩን ነው፡፡ የተጠናከረ የመረጃ ልውውጥ አለመኖራቸው፣ ተመሳሳይ ይዘት ያላቸው ስራዎች በተበታተነ መልኩ መሰራታቸውን እና ከባለድርሻ አካላት ጋርባለው የመረጃ ልዩነት ምክንያት ትክክለኛውን መረጃ ለማወቅ እና የገንዲ በሽታ በትክክል መቀነሱን ለመለየት አዳጋች ሁኔታን ፈጥሯል፡፡
- ✓ በተጨማሪም ከባለድርሻ አካላት ጋር በቆላዝንቦች እርባታ ወቅት ለሚከሰቱ ችግሮችወቅታዊ የሆኑ የምርምር ስራዎችን እንዳልተሰሩና ምንም ዓይነት የመረጃ ልውውጥ እንዳልተደረገ ለማወቅ ተችሏል፡፡ይህም በእርባታ ወቅት የሚከሰቱ ችግሮች ግልፅ ሆነው እንዳይወጡ ከማድረጉም በላይ ለሚከሰቱት ችግሮቹ አፋጣኝ መፍትሄ እንዳያገኝ እንደሚያደርገው ይታመናል፡፡

92.በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተሰጠው የማሻሻያ ሃሳብ ተግባራዊ የተደረገ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

93.በዲላ ጣቢያ ደረጃ ከባለድርሻ አካላት ጋር የልምድ ልውውጥ የሚደረግበት፣ መደበኛ የሆነና የተቀናጀ የመረጃ ልውውጥ ስርዓት የሌለ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

94. የመረጃ ልውውጥ ከ ደቡብ ክልል እና ከኦሮሚያ እንስሳትና ዓሳ ሀብት ልማት ጋር የመረጃ ልውውጥ እንዳላቸው፣ የመረጃ ልውውጡ በቃል እንጂ በመፃፃፍ እንዳልሆነ ከአርባምንጭ ማዕከል የስራ ኃላፊ ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ ታውቋል፡፡
95. ኢኒስቲትዩቱ ከባለድርሻ አካላት ጋር ያለው የልምድ ልውውጥ በግብረመልስ ያልተደገፈ በመሆኑ ከባለድርሻ አካላት የሚያገኘው ድጋፍ አናሳ ያደርገዋል፡፡

# ክፍል ሦስት

## መደምደሚያ

96. ኢኒስቲትዩቱ በበደቡብ ኢትዮጵያ ስምጥ ሸለቆ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ለመቆጣርና ለማጥፋት እየሰራቸው ያሉ ስራዎችብቃት ያለውና ውጤታማ እንዳይሆን እንቅፋት የሆኑ የአሰራር ድክመቶች ያሉበት መሆኑን በ2004 ዓ.ም በተደረገው የክዋኔ ኦዲት ከተገለፁት ሙሉ ለሙሉ በሚያስችል መልኩ አብዛኛዎቹ ያልተቀረፉ ሲሆኑ በክትትል ኦዲቱ ወቅትም አፅንዖት ተሰጥቷቸው መወገድ የሚገባቸው ችግሮች ያሉ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ እነርሱም ዋና ዋናዎቹ፡-

- ✓ ኢኒስቲትዩቱከ1990 ዓ/ም ጀምሮ እንቅስቃሴ የተጀመረ ቢሆንም እስከ 2008 ዓ/ም አጋማሽ ድረስበእቅዱ መሰረት በደቡብኢትዮጵያ ስምጥ ሸለቆ በቆላ ዝንብ ከተጠቃው 240,000 ካ.ኪ.ሜ ውስጥ 25,000 ካ.ኪ.ሜ ላይ የቆላ ዝንብን ነፃ አድርጓል ለማለት የማያስችል መሆኑ፣
- ✓ ኢንስቲትዩቱ ግቡን ለማሳካት የሚያስችሉ አመታዊ እቅድ አዘጋጅቶ በዓመታዊ ዕቅድ የተያዙ ስራዎች ስለመሰራታቸው የመመዘን፣ የክትትል፣ የግብረመልስ አሰጣጥ ክፍተቶች በመኖራቸው ጥንካሬና ድክመትን በጊዜ ለይቶ የእርምት እርምጃ እንዳይወስድ ማድረጉን ፣
- ✓ ለግዢ፣ ለሥራ ማስኪያጃና ለመሳሰሉት ተግባራት መዋል ከሚገባው የኢኒስቲቲዩቱ አመታዊ በጀት አብዛኛው ሥራ ላይ አለመዋሉ ኢኒስቲቲዩቱ ካለመው ግብ እንዳይደርስ ያደረገው መሆኑ እና ለታየው አዝጋሚ ለውጥ መንስኤ መሆኑ እንዲሁም ማዕከላት የተመደበላቸውን በጀት ባለማወቃቸውና በአንድ ጊዜ ባለመሰጠቱ አመጣጥነው መስራት ያለባቸውን ስራ እንዳይሰሩ እና የሚያስፈልጋቸውን ግዢ በወቅቱ እንዳያከናውኑ ማድረጉን፣
- ✓ ኢኒስቲትዩቱ በውጭ ምንዛሪ የሚገዛቸው የተለያዩ ግብዓቶች ማለትም የኬሚካል፣የታርጌት፣ወዘተ ግዢዎች በቅድሚያ ለበጀት ዓመቱ የሚያስፈልገው ግብዓት ታቅዶ ከማለቁ በፊት ተከታታይ የግዢ ትዕዛዝ ባለመሰጠቱ፣ አቅራቢ ድርጅቶች በገቡት የግዢ ውል መሠረት

ማቅረባቸውን ክትትልና ቁጥጥር ባለማድረጉና እንዲሁም በማዕከል ግዢ መፈፀም ባለመቻሉ ሥራው በታቀደው መሠረት እንዳይከናወን ማድረጉን፣

- ✓ በኢንስቲትዩቱ የተጠናከረ የንብረት አያያዝ ሥርዓት ባለመኖሩ በቃሊቲ ንብረት ክፍል ለመስክ አገልግሎት ሊውሉ የሚችሉ ብረቶች እንደ ቲባርአፕሊኬቱርና መሳሰሉት ተከማችተው ባሉበት ሁኔታ በክልል ባሉ ጣቢያዎች ላይ እጥረት አለ ተብሎ ግዢ መጠየቁ የሥራ አፈጻጸም ላይ ተፅዕኖ ማሳደሩን፣
- ✓ ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ ንብረቶችን ጠግኖ በስራ ላይ እንዲውል አለማድረጉ ወይም ህግና መመሪያ በሚያዘው መሰረት በወቅቱ አለማስወገዱ ፣ በእቃ ማከማቻ መጋዘኖች የቦታ ጥበት በመፍጠር ለአላስፈላጊ የመጋዘን ኪራይ እንዲዳረጉ ማድረጉን፣
- ✓ በኢኒስቲቲዩቱ ውስጥ በአንድ በኩል አዳዲስ የተገዙ እቃዎችና መሳሪያዎች ከሁለት ዓመታት በላይ በመጋዘን ውስጥ ያለአገልግሎት መቀመጣቸው፣ በሌላ በኩል ደግሞ በኢኒስቲትዩቱ መጋዘን ውስጥ የሚገኙ መሳሪያዎች በክልል ማዕከል/ጣቢያ የሚፈለጉ መሆኑ ኢኒስቲትዩቱ በመጋዘኑ ውስጥ ያሉትን ንብረቶች እንደማያውቅ እና በጥናትና ፍላጎት ላይ የተመረኮዘ ግዥ እንደማያካሂድ የሚያመለክት መሆኑ፣
- ✓ በኢኒስቱዩቱ በመስክ አገልግሎት ላይ የሚሳተፉ ማህበረሰቦችን መምረጫ መስፈርት/መመሪያ/ የሌለ በመሆኑ የኬሚካል እርጭት፣ እና የታርጌት ተከላ ስራ በጥራትና በብቃት እንዳይሰራ ማድረጉን፣
- ✓ በኢኒስቲትዩቱ ለሚረቡ ዝንቦችም ሆነ ለመስክ አገልግሎት የሚውሉ የተለያዩ መሳሪያዎች ባለመሟላታቸው በኢኒስቲትዩቱ የቆላ ዝንብ ማጥፋት ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ተአኖ ማሳደሩን፣
- ✓ በኢኒስቲትዩቱአስራ ስድስት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሰማኒያ ስምንት ሺህ አስራ አንድ ብር ከሰማንያ ስድስት ሳንቲም / 16,988,011.86/ብር ከፍተኛ የመንግሥት ሀብት የወጣባቸው የቆላ ዝንብ ማራቢያአምስት ክፍሎች /ሞጁልስ/ ያለአገልግሎት መቀመጣቸው፣

- ✓ በቆላ ዝንብ አካባቢ የሚኖረው ማህበረሰብ ከፕሮጀክቱ የተገኘው ጥቅምና ጉዳት ምን ምን እንደሆነ በኢኒስቲትዩቱ ጥናት አለመደረጉ ኢኒስቲትዩቱ ያስገኘው ተጨባጭ ለውጥ ምን ምን እንደሆነ እንዳይታወቅ ማድረጉን፣
- ✓ በእንስሳት ጀርባ ላይ የሚቀባ ኬሚካል መጠን አጠቃቀም ስርዓት ባለመዘርጋቱ በከፍተኛ ወጪ በውጭ ምንዛሪ የተገዙ ኬሚካሎች እንዲባክኑ ማድረጉን፣
- ✓ በቆላ ዝንብን ለማጥፋት በመስክ ስራ ላይ ለሚሳተፉ የማህበረሰብ አካላት ወደ ሥራ ከመሰማራታቸው በፊት ተገቢው ሥልጠና አለመሰጠቱ ስራው በተገቢው መንገድ በጥራት እንዳይሰራ ማድረጉን፣
- ✓ በመስክ ሥራ ለእንስሳት መቀቢያ የሚያገለግሉ በአካባቢው ከሚገኙ ቁሳቁሶች የተሰሩ በረቶች ለስራ አመቺ ባለመሆናቸው የኬሚካል ብክንት እንዲፈጠር ማድረጉን፣
- ✓ በኢንስቲትዩቱየመረጃ አያያዝ ክፍተቶች በመኖራቸው ግልጽ፣ ወጥ የሆነና የማይጣረዝ መረጃ እንዳይገኝ ማድረጉን፣
- ✓ ኢኒስቲትዩቱ ከባለድርሻ አካላት ጋር ያለው የልምድ ልውውጥ በግብረመልስ ያልተደገፈ መሆኑ፣

# ክፍል አራት

## የማሻሻያ ሃሳቦች

97.በ2004 ዓ.ም ኢኒስቲትዩቱ የደቡብ ኢትዮጵያ ስምጥ ሸለቆ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ መቆጣጠሪያና ማጥፊያ አፈፃፀም በተመለከተ በተደረገው የክዋኔ ኦዲት ለኢኒስቲትዩቱ በቀረበው ሪፖርት ላይ የተሰጡ የማሻሻያ ሀሳቦች አብዛኛዎቹ አብዛኛዎቹ በሚፈለገው መጠን ተግባራዊ ያልተደረጉ እና ተጨባጭ ውጤት ያላስገኙ በመሆናቸው ኢኒስቲትዩቱ የተሰጡት የማሻሻያ ሀሳቦች ትኩረት ተሰጥቷቸው እንዲተገበሩ እንዲያደርግ በድጋሚ የሚከተሉት የማሻሻያ ሀሳቦች ቀርበዋል፡፡

- ✓ ኢኒስቲትዩቱየተለያዩ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቁጥጥር ዘዴዎችን አቀናጅቶ በመጠቀም ማለትም በእንስሳት ሰውነት ላይ ፀረ ቆላ ዝንብ ኬሚካል በመቀባት፣ መሬት ለመሬት ኬሚካል በመርጨት፣ በኬሚካል የተቀቡ የጨርቅ ወጥመዶችን ( ታርጌቶችን) በመትከል እና እንዳስፈላጊነቱ የአይሮፕላን የኬሚካል ርጭት በማካሄድ ፣ ለስራው ከፍተኛ ድጋፍ የሚያደርጉ ዓለም አቀፍና ሌሎች አጋር ድርጅቶች ድጋፋቸውን ከስራው ስፋትና መጠን ጋር በሚጣጣም መልኩ እንዲቀጥሉና በተለይ የዝንቦች ውጤታማነት ላይ የሚያተኩሩ ጥናታዊ ስራዎችና የአቅም ግንባታ ስራዎች እንዲቀጥሉ በማድረግ እና በመስክ ስራ የተሰማሩ ባለሞያዎች ስራቸው በአስቸጋሪ ጫካ ውስጥ እና ወንዞች አከባቢ ስለሆነ እነዲሁም በእርባታ ክፍል የሚገኙ ባለሞያዎች ስራቸውን የሚሰሩት በማይመች ሰው ሰራሽ አየር ውስጥ በመሆኑ ለባለሞያዎቹ የተለያዩ ጥቅማጥቅሞችን እና ማበረታቻዎችን በመስጠት ችግሩን ደረጃ በደረጃ በመቀነስ ብሎም ማጥፋትና ለእንስሳትና እርሻ ልማት ምቹ የሆነ አከባቢ ለመፍጠርይቻላል፡፡
- ✓ ኢንስቲትዩቱ ጥንካሬውንና ድክመቱን በጊዜ ለይቶ የእርምት እርምጃ ለመውሰድ ግቡን ለማሳካት የሚያስችሉ አመታዊ እቅድ አዘጋጅቶ በዓመታዊ ዕቅድ የተያዙ ስራዎች ስለመሰራታቸው ክትትልና ግምገማ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

- ✓ ኢኒስቲትዩቱ ለግዢ፤ ለሥራ ማስኪያጃና ለመሳሰሉት ተግባራት ከመንግስት የሚመደብለትን በጅት ሙሉ ለሙሉ ስራ ላይ ለማዋል የሚሰራቸውን ስራዎች አመጣጥኖ በእቅዱ መሰረት ማከናወን እንዲሁም ክልል ለሚገኙ ማዕከላትና ጣቢያዎች የሚመደብላቸው በጀት እንዲያውቁት በማድረግ በወቅቱ ወደተከፈተላቸው አካውንት ገቢ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ✓ ኢኒስቲትዩቱ በውጭ ምንዛሪ የሚገዛቸው የተለያዩ ኬሚካሎች እና መሳሪያዎች በቅድሚያ ለበጀት ዓመቱ የሚያስፈልገው መሆኑን መለየት፣ እቃው ወይም ኬሚካሉ በመጋዘን ውስጥ አለመኖሩን ማረጋገጥ ፣ወቅቱን የጠበቀ ተከታታይ የግዢ ትዕዛዝ መስጠት፣ የሚገዛቸውን እቃዎች ለመንግስት ግዢና ንብረት አወጋገድ ኤጀንሲ ማሳወቅ እና አቅራቢ ድርጅቶች በገቡት የግዢ ውል መሠረት ማቅረባቸውን ክትትልና ቁጥጥር ቢያደርግ ሥራው በታቀደው መሠረት እንዲከናወን ያስችለዋል፡፡
- ✓ ኢንስቲትዩቱየተጠናከረ የንብረት  አያያዝ እንዲኖረው ያሉትን የተለያዩ ንብረቶች በቢን ካርድ መመዝገብና በእቃዎች ላይ ማስቀመጥ ፣ያሉትን ንብረቶች በዋጋቸው መዝግቦ በተደራጀ ሁኔታ መያዝ፣ እና ሰፊና አመቺ መጋዘኖችን መጠቀምይኖርበታል፡፡
- ✓ ኢኒስቲትዩቱ ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ ንብረቶችን ህግና መመሪያ በሚያዘው መሰረት በወቅቱ ለሚመለከተው አካል በማቅረብ እናበማስወገድ ያለበትን የመጋዘን የቦታ ጥበት ለመቅረፍ ይችላል፡፡
- ✓ ኢኒስቲቲዩቱ አግልግሎት መስጠት እየቻሉ ያለአገልግሎት የተቀመጡ የተለያዩ ንብረቶችን ለመስክ ስራ የሚያገለግሉትን እና ለእርባታ ክፍል የሚያስገልጉትን ለይቶ በማውጣትና አግልግሎት ላይ እንዲውሉ በማድረግ ንብረቶቹ በመቀመጥ ብዛት እንዳይበላሹ፣ ንብረቶች በመጋዘን እያሉ ድጋሚ ግዢ እንዳይፈፀም እና ኬሚካሎች፣ ሌሎች የላብራቶሪ እቃዎችና ግብዓቶች የመጠቀሚያ ጊዜያቸው እንዳያልፍ፣ ለማድረግ ይረዳዋል፡፡
- ✓ ኢኒስቱዩቱ የኬሚካል እርጭት፣ እና የታርጌት ተከላ ስራ በጥራትና በብቃት እንዲሰራ በመስክ አገልግሎት ላይ የሚሳተፉ ማህበረሰቦችን መምረጫ መስፈርት/መመሪያ/ ማዘጋጀትይኖርበታል፡፡

- ✓ ኢኒስቲትዩቱ ለሚረቡ ዝንቦችም ሆነ ለመስክ አገልግሎት የሚውሉ የተለያዩ መሳሪያዎችንና ኬሚካሎችንቢያሟላ የቆላ ዝንብ ማጥፋት ሥራ እንቅስቃሴ ፈጣንና ውጤታማ እንዲሆን ያስችለዋል፡፡
- ✓ በኢኒስቲትዩቱ አስራ ስድስት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሰማኒያ ስምንት ሺህ አስራ አንድ ብር ከሰማንያ ስድስት ሳንቲም / 16,988,011.86/ ብር ከፍተኛ የመንግሥት ሀብት የወጣባቸው የቆላ ዝንብ ማራቢያ አምስት ክፍሉች /ሞጁልስ/ ስራ ላይ ሊውሉ ይገባል፡፡
- ✓ ኢኒስቲትዩቱ በቆላ ዝንብ አካባቢ የሚኖረው ማህበረሰብ ከፕሮጀክቱ የተገኘው ጥቅምና ጉዳት ምን ምን እንደሆነ በየሶስት ዓመቱ ጥናት ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ✓ ኢኒስቲትዩቱ በእንስሳት ጀርባ ላይ የሚቀባ ኬሚካል መጠን አጠቃቀም ስርዓት ቢዘረጋ በከፍተኛ ወጪ በውጭ ምንዛሪ የተገዙ ኬሚካሎች እንዳይባክኑ ይረዳል፡፡
- ✓ ኢኒስቲትዩቱ በቆላ ዝንብን በማጥፋት ስራ ላይ ለሚሳተፉ የማህበረሰብአካላት / ባለሞያዎች/በየጊዜው ተገቢውን ሥልጠና ቢሰጥ የሠራተኞችክህሎት እንዲዳብር ይረዳል፡፡ይህ ደግሞ ኢኒስቲትዩቱ በእቅድ የያዛቸው ስራዎች በተገቢው መንገድ በጥራት እንዲሰሩ ያስችሏል፡፡
- ✓ በመስክ ሥራ ለእንስሳት መቀቢያ የሚያገለግሉ በአካባቢው ከሚገኙ ቁሳቁሶች የተሰሩ በረቶች ለስራ አመቺ ቢሆኑበከብቶች ላይ ኬሚካል የመቀባት ስራ ፈጣን እንዲሆን እና የኬሚካል ብክንት እንዲቀንስ ይረዳል
- ✓ በኢንስቲትዩቱ የተጠናከረ የመረጃ አያያዝ ስርዓት ቢዘረጋ ግልጽ፣ ወጥ የሆነና የማይጣረዝ መረጃ እንዲኖር ይረዳል፡፡
- ✓ ኢኒስቲትዩቱ ከባለድርሻ አካላት ጋር ያለው የልምድ ልውውጥ በግብረመልስ የተደገፈ ሊሆን ይገባል፡፡

በመጨረሻም የኢኒስቲትዩቱ ኃላፊዎች እና ሰራተኞች በክትትል ኦዲቱ ወቅት ስላደረጉልን የቀና ትብብር እናመሰግናለን፡፡

# <u>አባሪ 1</u>

## በኦዲቱ ወቅት የተሰጡ የማሻሻያሀሳቦች

*ፕሮጀክቱበተዘጋጀለትእቅድመሠረትኢኮኖሚያዊናብቃትባለውመንገድ መከናወኑንናአላማውንስኬታማማድረጉንበተመለከተ፣*

- *በኢትዮጵያ በቆላ ዝንብ ከተጠቃው 240,000 ካ.ኪ.ሜ ውስጥ በደቡብ ኢትዮጵያ የሚገኘውን 25,000 ካ.ኪ.ሜ ላይ የቆላ ዝንብን ነፃ ለማድረግ እንዲያስችል በያዘው የ5 ዓመት ዕቅድ ላይ ከባለ ድርሻ አካላት ጋር በተናጠልም ሆነ በጋራ ልዩ ትኩረት በመስጠት አስቸኳይ የመፍትሄ እርምጃዎችን መውሰድ ይገባል፡፡የመፍትሄ እርምጃዎቹም በእርባታ ማዕከሉም ሆነ በመስክ የሚያጋጥሙ የተለያዩ ችግሮችን ለይቶ ማውጣትና ለችግሮቹ ከሚመለከተው አካል ድጋፍ በመጠየቅ አፋጣኝ መፍትሄ መውሰድ፣በጉዳዩ ላይ ከባለ ድርሻ አካላት ጋር መወያየትና የትብብርና የቅንጅት ስልት በመንደፍ ተግባራ ዊማድረግ፣በማዕከሉ በተለይ በዕርባታ ክፍል ውስጥ የሚሰሩ ባለሞያዎች እና በመስክ ስራ ለሚሳተፉ አካላት ከስራው አድካሚነት የተነሳ የሚበረታቱበት ዘዴ የመንደፍና ተግባራዊ የማድረግ፣መንግስታዊ ያልሆኑና ለትርፍ ያልተቋቋሙ ድርጅቶች ተሳታፊ የሚሆኑበትን መንገድ የማመቻቸት ተግባራት ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል፡፡*
- *በማዕከሉ ሊተገበር የሚችል ዕቅድ የማዘጋጀት፣በዕቅዶች ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር መወያየትና የትብብርና የቅንጅት ስልት መንደፍና፣ተገውን አቅም ግንባታ ሥራ በመሥራት እና በዕቅድ የተያዙ ስራዎች ስለመሰራታቸው ክትትልና ግምገማ የማድረግ ሂደት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡*
- *ለፕሮጀክቱከመንግሥትየሚመደበውንበጀትየመፈጸምናየመጠቀምአቅምማጐልበት፣*
- *የፕሮጀክቱን ንብረት የመንግሥት መመሪያን በመከተል በአግባቡ መዝግቦ መያዝ፣ አጠቃቀሙንም ማሻሻልና ጥቅም ላይ ሊውሉ የማይችሉትን በወቅቱ የመንግሥት ንብረት አወጋገድ ሥርዓትን ተከትሎ ማስወገድ ይኖርባቸዋል፡፡*
- *በፕሮጀክት ማዕከሉ በቆላ ዝንቦች እርባታ ወቅት የሚከሰቱ የሞት አደጋዎች ዓይነትና ለችግሩ የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎችን በተመለከተ፣በፕሮጀክት ማዕከሉ የእርባታ ክፍሉን በማስመልከት የሚደረጉ ስብሰባዎች ላይ የሚደረጉ ውይይቶችና*

የተነሱ ችግሮችን የሚገልጹ መረጃዎች ሊያዙ ይገባል፡፡በተጨማሪም ከተለያዩ ምንጮች የሚገኙ የቆላ ዝንብና የገንዲ በሽታን የሚመለከቱ መረጃዎችን አሰባስቦና አደራጅቶ ለምርምርነት መጠቀም እና ለሌሎች መረጃውን ለተለያየ ግብዓት ለሚፈልጉ አካላት በቀላሉ የሚያገኙበትም ሆነ የሚሰራጭበት መንገድ ለማመቻቸት የሚያስችል የመረጃ አያያዝና አቅርቦት ሥርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

- ❖ ግንባታቸውየተጠናቀቁ 5ት የቆላ ዝንብ ማራቢያ ክፍሎች በማቴሪያል ተሟልተውስራ የሚጀምሩበት መንገድ ሊመቻች ይገባል፡፡
- ❖ የቆላ ዝንቦችን ለመቀነስ የተጀመረው የመሬት ለመሬት የኬሚካል እርጭት ተግባር ሊቀጥልና በፖርኮች አካባቢበ አውሮውፕላን ሊደረግ የታሰበው የኬሚካል እርጭትተግባር በቅርብ ጊዜ ሊከናወን እና ስለ ተግባራዊነቱ ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡
- ❖ በቆላ ዝንብ አካባቢ የሚኖረው ማህበረሰብና አካባቢ ከፕሮጀክቱ የተገኘው ጥቅምና ጉዳት በተቀመጠው መርሃ-ግብር መሠረት በየሶስት ዓመቱ ጥናት ሊደረግና በመረጃነት ሊያዝ ይገባል፡፡ይህም ፕሮጀክቱ የተሰሩና ያልተሰሩ ስራዎችን በደንብ ለይቶለማወቅናመረጃን ለበላይ አካላት ለማቅረብ ከመርዳቱም በላይ አስፈላጊውን እርምጃዎች በወቅቱ ለመውሰድ ያስችላል፡፡
- ❖ በመስክ አገልግሎት ላይ የሚሳተፉ ማህበረሰቦችን መምረጫ መስፈርት/መመሪያ/ እና አገልግሎት የሰጡ የኬሚካል ዕቃዎች በተለያየ መንገድ እንዳይወገድና አንድ ወጥ የሆነ የማስወገጃ ዘዴ እንዲኖር መመሪያዎች ተዘጋጅተው ለሚመለከታቸው አካላት/ለጣቢያዎች/ ማሰራጨትና ስለተግባራዊነቱ ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡
- ❖ ኬሚካሎች የሚገዙት በውድ እና ለቆላ ዝንብ ቅነሳ ስራ ከሚያገለግሉት ውስጥ አንዱ በመሆኑ የተገዙትን ኬሚካሎች ከብክነት ለመጠበቅ አስፈላጊ መሣሪያዎችና ስለአጠቃቀሙ መመሪያዎች ተዘጋጅተው ሥራ ላይ ሊውሉ ይገባል፡፡ይህም የኬሚካል መለኪያ /Aplicator/ ሚያገለግለው መሳሪያ በብቃት በመግዛት በሁሉም ጣቢያዎች የኬሚካል ቅቢውን በመሳሪያው ብቻ እንዲቀቡ ማድረግ፣የርጭት ተግባሩን ከከብቶች ጋር የሚመጣጠን በረት በመስራት ከበረት ውጪ እንዳይቀቡ ማድረግ እና በርጭት ተግባሩ ላይ የሚሳተፉ የማህበረሰብ አካላትን ተከታታይነት ያለው ስልጠና በመስጠት ከብክነት መከላከል ስለሚቻል ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት ሊሰራ ይገባል፡፡

- በግዢ መዘግየት ምክንያት በዕርባታ ማዕከሉም ሆነ በመስክ ስራ ላይ ችግሮች እንዳይከሰቱ ከሀገር ውስጥም ሆነ ከውጪ ሀገር የሚደረጉ ግዢዎች ሊፋጠኑ ይገባል፡ ፡የግዢ ሂደቶችም በለጋሽ አካላት የሚደረጉትም በፍጥነት በመፃፃፍ እንዳይዘገዩና የሀገር ውስጥዕ ቃዎችም ግዢ ተጠይቆ ሳይቆዩ ትኩረት ተሰጥቷቸው በቶሎ ሊፈፀሙ ይገባል፡፡
- በዕርባታ ማዕከሉ የሚታዩ የመሰላቸት፣የግዴለሽነት እና በመስክ አካባቢ የታርጌቶችን ነቅሎ መውሰድ፣ኬሚካል በአግባቡ አለመቀባት የመሳሰሉ ችግሮችን ለማስወገድ በማዕከሉ ለሚያገለግሉ ባለሞያዎችም፣በመስክ ስራ ላይ ለሚሳተፉና በአካባቢው ለሚኖሩ የማህበረሰብ አባላት ተከታታይነት ያለው የግንዛቤ ስራ ሊሰራና የተገኘው ለውጥ ላይ ክትትል የሚደረግበት ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

በመጨረሻም የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ኃላፊዎችና ሠራተኞች፣የመስክ ኦፕሬሽን የማስተባበሪያ ቢሮ እና በስሩ ለሚገኙት 3ቱም /ወላይታሶዶ ፣አርባ ምንጭ እና ዲላ/ ጣቢያዎች እንዲሁም በኦዲቱ ወቅት መረጃ የተሰበሰበበት የክልል ግብርና ቢሮ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች ስላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡